# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን

# የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎችን እንቅስቃሴ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ** **ገጽ**


**ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMARY)** ........ 3

**ክፍል አንድ** ........ 8

- መግቢያ ........ 8
- ተቋማዊ ዳሰሳ ........ 9
  - የባለስልጣኑ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር ........ 9
  - የባለስልጣኑ ተግባርና ሥልጣን ........ 10
  - የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........ 11
  - የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ ........ 12
- የኦዲቱ ዓላማ ........ 12
- ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ ........ 12
- የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች ........ 12
- የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 13
- የኦዲቱ ዘዴ ........ 13
- የሥራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ........ 15

**ክፍል ሁለት** ........ 16

- ግኝቶች ........ 16
  - *የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ* ........ 16
  - *በዕቅድ አፈጻጸሙ ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራን በተመለከተ* ........ 19
  - *ጭነቶቹ ባህር ወደብ ከመድረሳቸው በፊት የውል ስምምነትን በተመለከተ* ........ 21
  - *ከባለድርሻ አካላት ጋር የለው የጋራ ውይይትን በተመለከተ* ........ 22
  - *የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማን በተመለከተ* ........ 23
  - *የመረጃ ማዕከል ማደራጀትን በተመለከተ* ........ 25
  - *በባህር ወደብ ላይ የቆዩ ገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ* ........ 26
  - *የዲመሬጅ ክፍያ መረጃ አያያዝን በተመለከተ* ........ 28
  - *ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ* ........ 29
  - *ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ* ........ 30
  - *እቃዎችን በወቅቱ የማያነሱ አስመጪዎች ላይ የእርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ* ........ 33
  - *በባህር ወደብ ላይ የተተው ዕቃዎችን በተመለከተ* ........ 35
  - *የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነትን በተመለከተ* ........ 36

**ክፍል ሦስት** ........ 41

- መደምደሚያ ........ 41

**ክፍል አራት** ........ 44

- የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 44
- አባሪ-1 ........ 47
  - *የማሪታይም ባለሥልጣን መዋቅራዊ አደረጃጀት* ........ 47
- አባሪ-2 ........ 48
  - *የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)* ........ 48
- አባሪ-3 ........ 53
  - የሥራ ሂደት መግለጫ/ Process Description ........ 53

**ማጠቃለያ (Executive summary)**

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎችን እንቅስቃሴ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 እና የ2009 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ሥራ ክንውኖችን በማከተት ነው፡፡

በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/99 መሠረት ሲቋቋም በገቢና ወጪ፣ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደው የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን መቆጣጠር፤ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግና ማስተባበር፤ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና ወጪው እንዲቀንስ፣ ዕቃዎች በወደቦች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማስተባበርና መምራት፤ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፤ የባህርና የአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ የሚያድረጉበትን መንገድ መፈለግ፡፡ የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ከፍተኛ ደኅንነት እንዲኖረው ማረጋገጥ፤ በአገሪቱ የዳበረና ቀጣይነት ያለው የማሪታይም ዘርፍ ክሕሎት እንዲኖር ማድረግ እና ከዓለም አቀፍ የማሪታይም ዘርፍ ስምምነቶች ጋር በተያያዘ ሀገሪቷ መፈጸም ያለባትን ግዴታና ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ተከታትሎ ማስፈጸም እንደሚገባ ተጠቅሷል፡፡

የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 549/99 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ባለመተግበራቸው የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከከፍተኛ መጠን ጭነት አስመጪዎች (ከስኳር ኮርፖሬሽን፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ከግብርና ምርት ማሳደግያዎች አቅርቦት ዘርፍ እና ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትና ከሌሎች አስመጪዎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት) የከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብር ዕቅድ ለመዘጋጀት የሚያስችል ማስረጃዎችን ወጥና አግባብ በሆነ መልኩ በደብዳቤ ስለመሰበሰቡ ተጠይቀው የ2006 ዓ.ም፤የ2007 ዓ.ም እና የ2009 ዓ.ም ብቻ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቀሪው የ2008 ዓ.ም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ባለስልጣኑ በየበጀት ዓመቱ ተዘጋጅቶ ጸድቋል የተባለው የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድ መረሃ- ግብር /Schedule/ ዝግጅት ላይ ከአስመጪዎች፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሰዋል የተባለ ቢሆንም ይህ ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ በኦዲት ወቅቱ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በባለስልጣኑ በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርኃ-ግብር ለአስመጪዎች በወቅቱ እንደሚደረሳቸውና በዕቅድም መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች መካከል ለኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ለኢትዮጵያ ነደጅ አቅራቢ ድርጅት እና ለአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጅክት ጽ/ቤት በባለስልጣኑ የሚዘጋጅ አመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሃ ግብር የማይደረሳቸው መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ እቅዱንና የአፈጻጸም መርሃ-ግብሩን በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ አዘጋጅቶ ለሚመለካታቸው አካላት በየጊዜው የማይልክ መሆኑ፤
- በብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና በመርሃ-ግብሩ መሠረት ከባህር ወደብ በወቅቱ ዕቃዎቻቸውን ወደ ሀገር ለሚያስገቡ አስመጪዎች፤ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተለይተው ተገቢው ግምገማ በማድረግ በባለስልጣኑ ዕውቅና የማይሰጥ መሆኑን በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች ከኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን፤ ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅትና ከግብርና ምርት ማሳደግያና አቅርቦት ዘርፍ ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በባለስልጣኑ ደረጃ ከሚመለከታቸው የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃን በየዕለቱ ለማሰባሰብና በአንድ ማዕከል ለመያዝ የሚያስችል ዳታ ሲይሰተም (Data system) ባለመኖሩ አሰፈላጊና ወቅታዊ የሆኑ የሎጂስቲክስ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ ለማሳራጨት አለመቻሉን፤
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሀገራዊ የሆነ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በተመለከተ በኢ-ሜይል በየቀኑ ከተለያዩ ዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች ለባለስልጣኑ ሲላክ የነበረው በ2006 ዓ.ም መ/ቤቱ ሥራ ላይ አውሎት የነበረ ሶፍትዌር የገቢና ወጪ ዕቃዎችን ኦፕሬሽን ሙሉ መረጃ ከዕቃ አስተላላፊ

ድርጅቶች ተቀብሎ እና አጠናቅሮ ለባለስልጣኑ የሚያሳውቅ የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ተዘርግተው የነበረ ቢሆንም ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራው ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ መሆኑ፤

- በባለስልጣኑ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚገቡ የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ ማስረጃዎቹ ለመጠናከርና ዕቃዎቹ የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለመለየት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤
- ባለስልጣኑ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች፣ ዕቃ አስተላላፊዎች፣ መርከብ ወክሎችና ሌሎች አካላትን መረጃ አጠናቅሮ የማይያዝና ድርጅቶችን ተጠያቂ የሚያደርግበት የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፤
- በ2006 ዓ.ም የከፍተኛ መጠን ገቢ ጭነት አገባብ ኦፕሬሽናል ዕቅድ በሚል በተዘጋጀ ዶክሜንት መሠረት የስቶሬጅና ተዛማጅ የወደብ ክፍያዎችን በተመለከተ እ.አ.አ ከጥር 2012 እስከ ሰኔ 2013 የከፍተኛ መጠን ጭነት ብቻ 38,522,598.11 የአሜሪካን ዶላር የተከፈለ ሲሆን የፕሮጅክት ካርጎ ደግሞ 4,120,246.10 በድምሩ 42,642,844.21 የአሜሪካን ዶላር ቢሆንም በችግሩ ዙሪያ ትንታኔ በመስጠት ውጤቱን በሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግስት አካላት ያልቀረበ መሆኑ፤
- በ2008 ዓ.ም የደረቅ ብትን ጭነት ሎጅስቲክስ ፕሮግራም በሚል በቀረበው ጥናት የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት ለመርከብ ዲመሬጅ ብቻ በበጀት አመቱ ዝቅተኛ ስሌት ቢያንስ 5.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በአጠቃለይ የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት የሎጅስቲክስ ወጪ ዓመታዊ አማካኝ 257.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይም 5.6 ቢሊዮን ብር መሆኑን ያሚያስረዳ ቢሆንም የተካሄደውም ጥናት በጥቅል የቀረበና አላግባብ የወጣውን ወጪ በማን እንደሆነ ዝርዝር መረጃ ያልያዘ መሆኑና በወቅቱም ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤
- በተጨማሪም በ2008 ዓ.ም በዩኒሞዳል በሚጓጓዙ የጀነራል ካርጎ ጭነት ላይ የብትን ጭነት ኦፕሬሽን ባስከተለው ጫና ምክንያት ለተጨማሪ ብር 162.1 ሚሊዮን ወጪ መሆኑ፤

- ሀገሪቷ በየዓመቱ በዲመሬጅ ምክንያት ወጪ የምታደርገውን የውጭ ምንዛሪ ክፍያን በተመለከተ መረጃው በባለስልጣኑ ባይያዝም በጅቡቲ የሚገኝ በገቢ.ዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሙሉ መረጃ እንደሚያዝ የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ የገለጹ ቢሆንም በጅቡቲ የኢትዮጵያ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በጂቡቲ በተደረገው መስክ ጉብኝት ወቅት በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በስጡት መልስ የዲመሬጅ ክፍያ ዝርዝር መረጃው በጅቡቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩልም የማይያዝ መሆኑ፤
- የባለሰልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ስለባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃውን በተመለከተ  በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጅቡቲ የሚገኝ የኢትዮጵያ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንደሚያዝ ቢገልጽም፤ ነገር ግን ኦዲት ቡድኑ በጂቡቲ በካሄደው መስክ ጉብኝት ወቅት የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በስጡት መልስ አሁን ባለው አሰራር ከተለያዩ የመርከብ ወክሎች የሚሳጥ ማኒፌስት የዩኒሞዳል እና የመልቲሞዳል ተጠቃልሎ የሚላክበት ሁኔታ በመኖሩና የሚጠቀሙበት የአስኩዳ ሲስተም የባለስልጣን መ/ቤት ሰርቨር ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ሲስተሙ የፖርት ፖዝሽን ሪፖርት የማያወጣ በመሆኑ የማይቀርብ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በባህር ወደብ ላይ በወቅቱ የማይነሱ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ የከፍተኛ መጠን ጭነት የሆኑ ገቢ ዕቃዎች (ከሰል ድንጋይ፤ስኳር፤ብረትና ስንዴ እና የተለያዩ ኮንንቴነሮች) ለባለስልጣኑ በባህር ወደብ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ሪፖርት የሚቀርብ (port position) ቢሆንም ሪፖርቱ በትክክል ዕቃዎቹ በዝርዝር መቼ እንደተራገፉና ከባህር ወደብ እንደተነሱ፤ በወደብ ላይ የቆዩበት ትክክለኛ የሆነ ቀናት የማያሳይ መሆኑ፤
- ባለ-ሥልጣኑ በባህር ወደብ ላይ በወቅቱ  ወይም ከዕፎይታ ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ የሚቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ የገቢ ዕቃዎችን መረጃ በማጠናከርና በመተንተን ውጤቱን ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ በሪፖርት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለመላኩ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- በባህር ወደብ ላይ የተተዉ እቃዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎችን ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ግማሽ ዓመት የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከ2010 እስከ 2015 እ.አ.አ ብቻ ያልተሟላ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያቀረቡ ሲሆን የተሰበሰበው መረጃ ሙሉና ወቅታዊ ባለመሆኑ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ ተተንትኖ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሪፖርት አለመደረጉ እና ከ2016 እስከ 2017 ግመሽ ዓመት ያለው መረጃ ግን ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- በ1994 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 284/94 የጸደቀው የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት፣በክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት ሁለቱም ሀገራት ካርጎ/ዕቃ በባህር ወደብ ከተረጋፈ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ቀናት ብቻ ለገቢ ዕቃዎች ያለምንም ክፍያ /30 days are Grace period for Import Transit Cargo/ በባህር ወደብ መቆየት እንደሚቻል ቢገልጽም በአሁኑ ወቅት የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሻሻያ ያልተደረገ እና  የገቢ ዕቃዎች ያለክፍያ በባህር ወደብ መቆየት የሚችሉት ወይም የእፎይታ ጊዜ እስከ 8 ቀናት (8 days are Grace period for Import Transit Cargo) በመሆኑ አገሪቷ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ ለቆዩ ዕቃዎች ዲመሬጅ እየከፈለች መሆኑ፤
- በጅቡቲ ባህር ወደብ ታሪፍ መሠረት ገቢ ዕቃዎች/ ካርጎ በባህር ወደብ ላይ መቆየት የሚቻለው እስከ 8 ቀናት የእፎይታ ጊዜ /8 days are Grace period for import Cargo/ ሲሆን ሀገሪቷ ይህን የእፎይታ ጊዜ የተቀበለችበት የህግ አግባብ ወይም በሁለቱም ሀገራት መከካል የተሻሻለ የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት አለመኖሩ፤

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ከዘመናት በፊት በቀይ ባህር የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳየሉ:: ይህ የባህር ንግድ የሚካሄደው በአነስተኛ ጀልባዎች ሲሆን ሥርዓት ያለው ቁጥጥር የማይደረግበትና በማዕከል የማይመራ ነበር፡፡ በሀገራችን የባህር ትራንስፖርት ለሀገር ዕድገት ጠቃሚነቱና ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሆኑን ግንዛቤ ያገኘው ከኢጣሊያን ወረራ በኃላ ነው፡፡
2. ከዚህም የተነሳ የአሰብና የምጽዋ ወደቦችን በበላይነት የሚያስተዳድር በ1945 ዓ.ም የማሪታይም አስተዳደር በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡ ይኸው የማሪታይም አስተዳደር በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ደረጃዎች የነበሩት ሲሆን፣ በ1971 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 139/71 መሠረት የማሪታይም ትራንስፖርት ባለሥልጣን (Maritime Transport Authority) በሚል ስያሜ ተጠሪነቱ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሆኖ ራሱን የቻለ ባለሥልጣን መ/ቤት (Autonomous Public Authority) እንደገና ተቋቋመ፡፡ ይህ የባለሥልጣን መ/ቤት በተለይም የአሰብና የምጽዋ ወደቦችን ከማስተዳደር በተጨማሪ በወደቦቹ የስተቬደሪ[1]/ Stevedoring እና የሾርሀንድሊንግ/[2]shore handling አገልግሎቶችና የወደብ የዕቃ መገልገያ መሣሪያዎች የማከራየት አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡
3. በ1983 ዓ.ም በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ለውጥ ይህ መ/ቤት በዋናነት ተልዕኮው በወደብ ባለሥልጣን ላይ ያተኮረ ስለነበር አስፈላጊነቱ ስላልታመነበት ፈረሰ፡፡ ሆኖም የማሪታይም አስተዳደርን በተመለከተ የማሪታይም መምሪያ በትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር ስር በመምሪያ ደረጃና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ስር በመምሪያ ደረጃ ተዋቅሮ የወደብና የትራንዚት ጉዳዮችን የሚከታተል የወደብ ጉዳዮች መምሪያ ተቋቋመ፡፡ በዚህ መልኩ እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ቆይቶ፣ዘርፉ በተበታተነ መልኩ መመራቱ ብቻ ሳይሆን ባለቤት እንደሌለው ታይቶና የማሪታይም ዘርፍ ወጥ የመንግስት አካል የመኖር አስፈላጊነት ስለታመነበት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/99 መሠረት ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ተቋቋመ፡፡

---

[1] የማራገፍና የመጫን አገልግሎት

[2] ጭነቱ በወደብ ውስጥ መሬት ላይ ከተራገፈ በኂላ የሚሰጥ አገልግሎት

4. ኢትዮጵያ አዋሳኝ የሆኑት የጎረቤት ሀገሮች ወደቦች ከሰባት በላይ (አሰብ፤ ምፅዋ፤ ጂቡቲ፤ በርበራ፤ ፖርት ሱዳን፤ ሞቃዲሾ እና ሞምባሳ) ቢሆኑም፣ በጣም ውስን የሆነ የውጭ ንግድ በበርበራና በፖርት ሱዳን በኩል ከመተላለፍ በስተቀር በሙሉ ሊባል የሚችል የሀገራችን የገቢና የወጪ ዕቃዎች በጂቡቲ ወደብ እንደሚስተናገድ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሀገራችን የገቢና ወጪ ዕቃዎች ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሆነው ጭነት የሚጓጓዘው በባህር ትራንስፖርት ሲሆን የመተላለፊያ ኬላ ደግሞ የባህር ወደብ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡
5. ሀገሪቷ ከውጭ ከምታስገባቸው ገቢ ዕቃዎች ውስጥ በ2006 በጀት ዓመት በነበረው መረጃ መሰረት 57 በመቶ የሚሆነው ደረቅ፤ ፈሳሽ እና ብትን ጭነት ነው፡፡ ከአጠቃላይ ደረቅ ጭነት ውስጥ ደረቅ በልክ ጭነት 38 በመቶ ነው፡፡ ዋና ዋናዎቹ ብትን በልክ እና ደረቅ ጭነቶችም ማዳበሪያ፤ ስንዴ፤ ስኳር፤ ነዳጅ እና የድንጋይ ከሰል ሲሆኑ ከጀኔራል ካርጎ ደግሞ ብረታ ብረት፤ የመንግሥት የፕሮጅክት ማሽን ግብዓቶችን ጭምር በማስገባት ላይ ትገኛለች፡፡

# ተቋማዊ ዳሰሳ

## የባለስልጣን መ/ቤቱ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

### ራዕይ

6. በ2017 መጨረሻ በባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት የአፍሪካ ሞዴል መሆን፡፡

### ዓላማ

7. በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት ለባለስልጣኑ የተሰጡ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-
   - በገቢና ወጪ፣ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደው የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን መቆጣጠር፤ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግና ማስተባበር፤
   - በገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና ወጪው እንዲቀንስ፣ ዕቃዎች በወደቦች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማስተባበርና መምራት፤
   - የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፤ የባህርና የአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ የሚያድጉበትን መንገድ መፈለግ፡፡

- የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ከፍተኛ ደኅንነት እንዲኖረው ማረጋገጥ፤ በአገሪቱ የዳበረና ቀጣይነት ያለው የማሪታይም ዘርፍ ክሕሎት እንዲኖር ማድረግ እና
- ከዓለም አቀፍ የማሪታይም ዘርፍ ስምምነቶች ጋር በተያያዘ ሀገሪቷ መፈጸም ያለባትን ግዴታና ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ተከታትሎ ማስፈጸም፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

**የባለስልጣን መ/ቤቱ ተግባርና ሥልጣን**

8. ባለስልጣኑ በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል፡-
    - በገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የአገሪቷን የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋነት ማረጋገጥ፤መቆጣጠር፤ ማስተባበርና ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት፤
    - የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ መምራት፣ የባህር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚከሰቱ ችግሮች ተከታትሎ መፍትሔ መስጠት፣ መደራደር፣
    - በባህር ወደቦች የራሱ የመርከብ መጠጊያ እንዲኖረው መጣር፣ የደረቅ ወደብ ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት፣ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት፣ የመርከብና ሌሎች ጭነቶች ዋጋ ለመደራደር የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፣
    - ብሔራዊ የንግድ መርከብ እንዲጎለብት መጣር፣ አሰራሩን መቀጣጠር፣ ለባሕርና ለሃገር ውስጥ ውሃዎች ማመላለሻ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የስራ ፈቃድ መስጠትና መቆጣጠር፣
    - ማናቸውንም የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች ወይም መገልገያዎች መመርመርና መፍቀድ፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የሃገር ውስጥ ጉምሩክ ማስተላለፍያ ቦታዎችን አገልግሎቶች መቆጣጠር፣
    - የደረቅ ወደቦችን፣ የወደብ ዕቃ አስተላላፊዎችን፣ የመርከብ ወኪሎችንና የጉምሩክ አስተላላፊነትን ሥራ መቆጣጠር፣ ዝርዝር መመሪያዎችን ማውጣት፣ ሥራቸውን ማስተባበር ፣ አቅማቸውን ማጎልበት፣
    - ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል፣

- በማሪታይም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ የግል ባለሀብቶች የተቀናጀና የተደራጀ ተሳትፎ እንዲጎለብት ማገዝ፣ በማሪታይም ዘርፍ የሚደራጁ ማህበራትን ሥራ መቆጣጠር፣ የማሪታይም ዘርፍን የሚመለከቱ የንግድ ደረጃዎችን በትንታኔ በማስደገፍ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፣
- የደረቅ ወደቦችንና ሌሎችንም የውሃ ትራንስፖርት ነክ ጉዳዮችና ተግባሮች በማጥናት ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ በሚፈቀደው ፕሮግራም መሰረት ደረቅ ወደቦችና ሌሎችንም የሐመር መገልገያዎች ማቋቋም፣ ማሻሻልና መጠገን፤
- ባለሥልጣኑ በወደብ ክልል ውስጥና እንዲሁም ለባሕር ጉዞ ለሚያበረክተው ማናቸውም አገልግሎቶች ተገቢውን ዋጋ፣ ክራይ ወይም ሌላ ክፍያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ አጽድቆ ማስከፈል፤
- በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ረቂቅ መመሪያዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሁሉ በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ፤
- ውል መግባት፣ መክሰስና መከሰስ፣ ክርክሮችን በግልግል መጨረስና ለስራው እንደሚያስፈልገው ማንኛውንም ዓይነት ንብረት መግዛት፣ መሸጥ፣ ባለቤት መሆን፣ መከራየት ወይም ማከራየት፤
- የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

9. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር ሥር አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ ዘጠኝ ዳይሬክቶሬት፣ ሁለት ጽ/ቤቶች እና ሶስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመያዝ ተዋቅሯል፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሥራ ከጀመረው ከጂቡቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በስተቀር ሁለቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከአሁን ሥራ ያልጀመሩ ናቸው፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ መረጃ (በአባሪ 1) ተያይዟል፡፡

### የሰው ሀይል

10. ባለስልጣን መ/ቤቱ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) መሠረት ለባለስልጣኑ የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 218 ሲሆን፣ በ2009 ግማሽ በጀት ዓመት በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ብዛት 38 ወንድ እና 21 ሴት በድምሩ 59 ነው፡፡

### የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ

11. የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት ሲሆን፣ ከ2006 እስከ 2008 ዓ.ም. ያለው የበጀት አጠቃቀም መግለጫ በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | በጀት አመት | የተመደበው ብር | ስራ ላይ የዋለው ብር | በፐርሰንት (%) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2006 ዓ.ም | 9,291,200 | 7,424,756 | 80 |
| 2. | 2007 ዓ.ም | 12,687,120 | 10,815,463 | 85 |
| 3. | 2008 ዓ.ም | 22,806,800 | 12,266,294 | 53.8 |

## የኦዲቱ ዓላማ

12 ባለስልጣኑ ከተቋቋመበት አላማ አንፃር፣ በገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የአገሪቷን የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ

13 ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "በአገሪቱ ገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች

14 ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

- የሀገሪቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን የትራንዚት አገልግሎት አሰጣጥ በቁጠባ፤ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፤

- ➢ በባለስልጣኑ የሀገሪቱ ገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት አገልግሎትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርና የመረጃ ልውውጥ ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉት ናቸው፡፡

15 እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative critera) የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

16 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አገሪቱ የተፈራረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች፤ የገቢ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት መመሪያ፤ የገቢ ከፍተኛ ጭነት (Bulk Shipments) አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ፤ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) የጥናት ሰነድና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

16 ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች ( Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2001 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2009 ግማሽ ዓመት ድረስ ያለውን በአገሪቱ የሚካሄደውን የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜ፤ ወጪ እና ዕቃዎች ለታለመላት አለማ በወቅቱ እሰከሚደረሱ ድረስ ያሉ ጉልህ ዱዳዮች ነው፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

17 ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በማሪይታም ጉዳይ ባለስልጣን መ/ቤት ሲሆን፣ በናሙና በተመረጡት ተቆጣጣሪ ባለድርሻ አካላት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ አከናዋኝ /Operator/ ከሆነው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ዋና መ/ቤት እና ከድሬዳዋ ደረቅ ወደብ ቅ/ጽ/ቤትና ከሞጆ ደረቅ ወደብ ቅ/ጽ/ቤት፣ ከከፍተኛ መጠን ጭነት አስመጪዎች (ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት፤ ከኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፤ ከግብርና ምርት ማሳዳግያ አቅርቦት ዘርፍ፤ ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ

ፕሮጀክት ጽ/ቤት) እንዲሁም በጅቡቲ ባህር ወደብ ከሚገኙ የመንግስት አካላት፣ ከግል ዕቃ አስተላላፊና ከመርከብ ወኪል ድርጅቶች የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ሲሆን፣ እንዲሁም በቅ/ጽ/ቤቶቹ በአካል በመገኘት የኦዲት ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

## **የሥራ ሂደት መግለጫ** (Process Description)

18 ባለስልጣኑ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ጊዜና ወጪ እንድቀነስና ዕቃዎቹ ለታለመላቸው አላማ በወቅቱ እንዲደርሱ ለማድረግ ነው ፡፡ ይህን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር በዕቅድ እንዲመራ ለማድረግ፤ ከሁሉም አስመጪዎችና ከሚመለከታችው አካላት ለግብዓት የሚሆን ህጋዊ የእቅድ ማስረጃዎችን በማሰበሰብ፤ ሀገራዊ የሆነ አመታዊ ዕቅድ እና መርሃ-ግብር በመዘጋጀት፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስምምነት ላይ በማድረስ በማጽደቅ፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሕጋዊ በሆነ መልኩ መድረስ ነው፡፡ በአፈጻጸሙም ላይ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ከግኘ ጀምሮ በዩኒሞዳል የሚገቡ ገቢ ዕቃዎችን መረጃ በመሰብሰብና በመደረጃት በባህር ወደብ የመርከብ መደራረብ ለመስወገድ የወደብ አጠቃቀም ፕሮግራም መውጠትና ተግባራዊ በማድረግ፤ የጫኑ መርከቦችና በባህር ወደብ የተከመቹ ገቢ ዕቃዎች ከተወሳነላችው ጊዜ በላይ እንደይቆዩ ክትትልና ቁጥጥር በመድረግ ድጋፍ በመስጠት፤ በአፈጻጸሙ ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋር ተገቢ የሆነ ግምገማ በመድረግ በጽሁፍ ለሚመለከታችው ግብረ-መልስ በመስጠት፤ ከዕቅድ ውጪ ያስገቡትን አስመጪዎች ተገቢውን እርምት እርምጃ እንዲወሰድ መድረግና የላቀ ሥራ ለሚሳዩ ዕውቅና በመስጠት፤ጭነቶች በታሰበው ጊዜ ለታሰበው ዓላማና አገልግሎት እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ (Process Description) ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 3** ይመልከቱ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

19 ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነትን (Bulk Shipments) በተመለከተ ከአስመጪዎች መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን በየበጀት ዓመቱ የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) አመጣጥ መረሃ-ግብር ረቂቅ ዕቅድ በማዘጋጀት ከአስመጪዎች፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

20 በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከተሰጡት ዓላማዎች ማካከል አንዱ በገቢና ወጪ፣ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደው የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን መቆጣጠር፤ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግና ማስተባበር አንዱ ነው፡፡

21 ከዚህ አኳያ የአገሪቱ የገቢ ንግድ በሚፈለገው ደረጃ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ የተረጋገጠ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል እንዲሁም የገቢ ብትን ጭነት ብቻ ሳይሆን በአንድ ጊዜ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የገቢ ጭነት ክምችት በባህር ወደብ እንዳይኖር እና ተቀናጅቶ እንዲገባ የሚያደርግ የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በ2005 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

22 በዚህ መመሪያ መሠረትም ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነቶች (Bulk Shipments) መረጃዎችን የበጀት ዓመቱ በገባ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ከአስመጪዎች በመሰበሰብ እና በመተንተን የበጀት ዓመቱን ገዢ የሆነ/Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብር ረቂቅ ዕቅድ በማዘጋጀት ከአስመጪዎች፣ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ እና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ዕቅዱን በማጽደቅ፤ በዕቅድ መሠረት እንዲፈጸም ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ እንዳለበት ተገልጿል፡፡

23 ይሁን እንጂ ይህ ስለመከናወኑ በኦዲቱ ወቅት የቀረበ መረጃ በተከለሰበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል ፡-

➢ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከከፍተኛ መጠን ጭነት አስመጪዎች (ከስኳር ኮርፖሬሽን፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ከግብርና ምርት ማሳደግያዎች አቅርቦት ዘርፍ እና ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትና ከሌሎች አስመጪዎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት) የከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብር ዕቅድ ለመዘጋጀት የሚያስችል ማስረጃዎችን ከ2006 ዓ.ም. እስከ 2009 ዓ.ም. በደብዳቤ ስለመሰበሰቡ ተጠይቀው የ2006 ዓ.ም፤የ2007 ዓ.ም እና የ2009 ዓ.ም ብቻ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቀሪው የ2008 ዓ.ም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

➢ በባለስልጣን መ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድ መርሃ-ግብር /Schedule/ ተዘጋጅቶ የጸደቀ እና ከአስመጪዎች፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ስምምነት ላይ የተደረሰ ስለመሆኑ የተገለፀ ቢሆንም፣ይህ ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ በኦዲት ወቅት ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ በተጨማሪም ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ እቅዱን እና የአፈጻጸም መርሃ-ግብሩን በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ ወይም በመከለስ ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው የማይልክ መሆኑን በኦዲት ወቅት በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት እና ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማረዳት ተችሏል ፡፡

24 ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የብትን ጭነት መረጃዎች ከአስመጪዎች በደብዳቤ እና በኢሜይል ተጠይቆ በመሰበሰብና በማጠናቀር፤ፕሮግራሙ የሚዘጋጅና ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ውይይት በማድረግ ለአስመጪዎችና ለተቆጣጣሪ ተቋማት በኢሜይል የሚላክ መሆኑን፣ ወቅቱን ጠብቆም ዕቅዱ የሚከለስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25 ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተጠቀሰው በእያንዳንዱ ነባራዊ ሁኔታ ላይ እንደሚከተው መልስ አቅርቧል፡-

- ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ የብትን ጭነት መረጃዎችን ከአስመጪዎች በደብዳቤ እና በተዘጋጅው ፎርማት መሠረት የሚሰበሰብ ሲሆን በዋናነት ግን መረጃው መሰብሰብ ያለበት የግድ በደብዳቤ ብቻ ሳይሆን በኢ-ሜይልም ጭምር እንደሆነና ማስረጃውም በአባሪነት መያዙን የተገለጸ መሆኑ፤
- የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድ በባለስልጣኑ አስቀድሞ በተዘጋጀው ፎርማት መሠረት ከአስመጪዎች ከአሰባሰበ በኃላ የተጠቃለለ መርኃ-ግብረ ተዘጋጅቶ አስመጪዎችና ተቆጣጣሪ ተቋማት በተገኙበት ምክክርና ማሻሻያ በማድረግ ባለስልጣኑ እንደገና አጠናቅሮ በኢ-ሜይል ለሁሉም አስመጪዎች የሚያሰራጭ መሆኑና በአባሪነት የአስመጪዎች ፎርማ ማየት እንደሚቻል በበላይ ኃላፊው የተገለጽ መሆኑ፤

26 **የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎቹን** ከአስመጪዎች አግባብ ባለው ደብዳቤ ስለማሰብሰቡ ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ውይይት በማድረግ ስምምነት ላይ ስለመድረሳቸው ቃለ-ጉባኤ ወይም የስምምነት ሰነድ ስለመኖሩ እና ዕቅዱም በየጊዜው ስለመከለሱ የሚያስረዳ ማስረጃዎች በአባሪነት ተያይዟል ቢባልም መረጃዎቹን ከአስመጪዎች አግባብ ባለው ደብዳቤ ስለማሰብሰቡ የ2006 ዓ.ም፤የ2007 ዓ.ም እና የ2009 ዓ.ም ብቻ የቀረበ ሲሆን ቀሪው የ2008 በጀት ዓመቱን የከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብርና ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያስችል ባለስልጣን መ/ቤቱ ከአስመጪዎች ስለመሰበሰቡ ማስረጃዎችን በማውጫ ስብሰባ ወቅት አቀርባለው ባለው መሠረት የቀረቡ ደብዳቤዎች በ2008 ዓ.ም ውስጥ የመጋቢት እና የግንቦት ወር ውስጥ በግዥ አፈጻጸም ላይ ስለሚገኙ የብትን ጭነት (የአፈር ማዳበሪያ፤ስኳር፤የድንጋይ ከሰል፤ የምግብ እህል እና የእርዳታ ስንዴ) የተለከ ደብዳቤ እንጂ የበጀት ዓመቱን እቅድና መርሃ ግብር ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

27 በተጨማሪም ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስለአመታዊ እቅድና መረሃ-ግብርን ዝግጅትን በተመለከተ ከአስመጪዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ስምምነት ላይ ስለመድረሳቸው ቃለ-ጉባኤ ወይም የስምምነት

ሰነድ ስለመኖሩ በማውጫ ስብሰባ ወቅት የባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃዎች አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በተጻፈው መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ ሳይሆን ከኢ-ሜይል ፕሪንት የተደረገ ቃለ-ጉባኤው ስለመላኩ የሚያሳይ እንጂ የተላከው ቃለ-ጉባኤ የሌለ ከመሆኑ በተጨማሪ የተላከበት አድራሻ በግለሰቦች ኢ-ሜይል አድራሻ በመሆኑና የድርጅት አድራሻ/ኮርፖሬት ኢ-ሜይል/ ባለመሆኑ ማስረጃዎቹን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

28 በመሆኑም የአገሪቱን የወደብ አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊነት በማረጋገጥ የገቢና ወጪ ንግድ ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት የወጪ እና የጊዜ ፍጆታ በዘላቂነት ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት ለመተግበር አላስቻለም፡፡

**በዕቅድ አፈጻጸሙ ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራን በተመለከተ**

29 በባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቀውን የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ (National Bulk Shipments plan) ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ በወቅቱ በማሳወቅ በአፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

30 የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በ2005 በወጣው መመሪያ መሠረት ባለስልጣን መ/ቤቱ በጸደቀው ዓመታዊ ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ መሠረት እንዲፈጸም ተጨማሪ የአፈጻጸም መርኃ-ግብር አዘጋጅቶ በየሩብ ዓመቱ የመጀመሪያ አሥር ቀናት ውስጥ ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት በመላክ መርኃ-ግብሩን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን እንደሚከታተል ተገልጾል፡፡

31 በባለስልጣን መ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርኃ-ግብር ለአስመጪዎች በወቅቱ እንደሚደረሳቸውና በዕቅድም መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች መካከል ለኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ለኢትዮጵያ ነደጅ አቅራቢ ድርጅት እና ለአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጅክት ጽ/ቤት በባለሰልጣኑ የሚዘጋጅ አመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሃ ግብር የማይደረሳቸው መሆኑን በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

32 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለተጠቀሱ ተቋማት በሙሉ በየዓመቱ በየስድስት ወሩ ፕሮግራሙ ተዘጋጅቶ ለድርጅቶቹ በቋሚነት በኢ-ሜይል የተላከ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

33 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የከፍተኛ መጠን ጭነት የተጠቃለለ እና በአስመጪዎች ስምምነት የተደረሰበት መርኃ-ግብር በደብዳቤ እና በኢሜይል፤እንዲሁም በዌብሣይት ለአስመጪዎች ባለስልጣኑ ሲያዳርስ የቆየና ለአብነትም በኮ/70/ማጉ/663/06/06 በቀን 06/06/06 የተጻፈውን ደብዳቤና ለአስመጪዎች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የተላኩ መርሃ-ግብር መመልከት እንደሚቻል ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

34 ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ማስረጃዎቹ ለሚመለከታቸው አካላት ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም. ግመሽ ዓመት መርሃ-ግብር በድርጅቶች እና በአስመጪዎቹ ኮርፖሬት በሆነ አድራሻ/ኢ-ሜይል ሳይሆን በግለሰቦች ኢ-ሜይል አድራሻ/ስም በመሆኑና ግለሰቦቹ በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ቢለቁ ማስረጃዎቹ የድርጅቱ ማስረጃ ሆነው የማይቀጥሉ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

35 በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃዎችን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በጻፈው መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎቹ የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ በ2009 በታህሳስ ወር ለኢትዮጵያ ባህር ትራንዚት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የተለከው መሪሃ-ግብር እና ከኢ-ሜይል ፕሪንት የተደረገ **በተመሳሳይ ከላይ በቁጥር 34 ላይ በተጠቀሰው ውጪ ስላላቀረቡና** ዕቅዱም በየጊዜው ስለመከለሱ የሚያስረዳ ማስረጃዎችንም በተመለከተ የ2009 የጥር ወር የቀጣይ 6 ወራት መረሃ-ግብር ለአስመጪዎች መላክ ስለመጀመሩ የምያሰረዳ ማስረጃ ቢያቀረብም **ሌሎች የቀረቡ ማስረጃዎች** ከኢ-ሜይል ፕሪንት የተደረጉ መጻጻፎች እንጂ ስለመሪሃ-ግብሩ ክላሰ ባለመሆኑ ማስረጃዎቹ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

36 ይህ በመሆኑም በጸደቀው ዓመታዊ ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሂራዊ ዕቅድና መርሃ-ግብር መሠረት እንዲፈጸም ህጋዊ በሆነ መንገድ በየዓመቱ በመላክ እና በተጨማሪም በየጊዜው ወቅታዊ የሆነ የአፈጻጸም መርኃ-ግብር አዘጋጅቶ በየሩብ ዓመቱ የመጀመሪያ አሥር ቀናት ውስጥ

ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ባለመላኩ ምክንያት መርከቦች በአንድ ጊዜ ያለፕሮግራም ተደራርበው በመምጣት በወደብ ላይ ለረጅም ጊዜ እየቆሙ ይገኛሉ፡፡

**የአስመጪውና ዕቃ አስተላላፊ ውል ስምምነት ማሰባሰብን በተመለከተ**

37 የከፍተኛ መጠን ጭነት የባህር ወደብ ከመድረሱ  አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪዎች የዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን፣  በአገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ሊቀርብና ባለስልጣኑ የተገኘውን መረጃ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ልልክ ይገባል፡፡

38 የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በ2005 ዓ.ም በወጣ በመመሪያው አሰራር ስታንደርድ መሠረት የከፍተኛ መጠን ጭነትን በተመለከተ የባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪው የወከለው ዕቃ አስተላላፊ፤ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያው አጓጓዡን፤ በሀገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን አስመጪዎች ሲያቀርቡ ባለስልጣኑ የተገኘውን መረጃ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ይልካል የሚል ነው፡፡

39 ይሁን እንጂ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚገቡ የከፍተኛ መጠን ጭነትን በተመለከተ የባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪዎች  የዕቃ አስተላላፊ፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን፣ በአገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት ሰነድ መረጃ ባለሥልጣኑ መረጃዎችን ስለመሰብሰቡ እና ለሚመለከታቸውም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ስለማላኩ  በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ተጠይቀው ያልቀረበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

40 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይህ የባለስልጣን መ/ቤቱ ክፍተት መሆኑን የገለጹ ሲሆን ነገር ግን ለባለስልጣኑ ስለ ሀገር ውስጥ መጋዘን የተሰጠው ኃላፊነት አለመኖሩን ገልጸዋል ፡፡

41 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ከፍተኛ መጠን ጭነት 82% የሚሆነው የመንግሥት ስንዴ፤ማዳበሪያ እና ስኳር ሲሆን የወደብ ክሊራንስ እና የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት የሚሰጠው በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት በመሆኑ

መርከቦች ወደብ ከመድረሳቸው አስቀድሞ የአስመጪዎች ዶክሜንቶችንና ሌሎችን ጉዳዮች እንዲያሟሉ እና ቅጅ ለባለሥልጣኑ በቋሚነት እየተላከ እንደሚገኝና ሠነዶች/ደብዳቤዎች በአባሪነት እንደተያዙ ገልጸዋል፤፤

42 ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በ2005 ዓ.ም በወጣው በመመሪያ ገጽ 18 የአሰራር ስታንደርድ ስር ከተዘረዘሩት ተግባራት ውስጥ ቁጥር 6 እና 7 ላይ በተገለጸው የባለስልጣኑ ሥራ እንደሆነና የተባሉትም ሠነዶች/ደብዳቤዎች በአባሪነት ያልተያዙና የቀረቡም ቢሆን የውል ስምምነት ሳይሆን በባህር ወደብ ስለተከመቹ ዕቃዎችን በተመለከተ ደብዳቤዎች ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

44 የተዘጋጀው ከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድና መርሃ ግብር ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በወቅቱ በማሳወቅ በአፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ባለመድረጉ ምክንያት በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚገቡ ዕቃዎችን የጫኑ መርከቦች በአንድ ጊዜ ወደ ወደብ ተደራርቦ በመምጣት ሀገሪቷን ለተጨማሪ መርከብ ዲመሬጅ[3]/Demurrage/ እና መጋዘን ወጪ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ከመደረጉም በላይ ዕቃዎቹ ለተፈለገው ዓላማ በወቅቱ እንዳይውሉ አድርጓል፤

## ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የጋራ ውይይትን በተመለከተ

43 ባለስልጣኑ መ/ቤቱ በየወቅቱ የገቢ ከፍተኛ ጭነት አፈጻጸም ግምገማን በተመለከተ ከአስመጪዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

44 የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በወጣው መመሪያ ላይ የጸደቀ ዓመታዊ ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ በየደረጃው ግምገማ የሚያደርግበት እና ወቅታዊ ጉዳዮችና በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ባለስልጣኑ ከአስመጪዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የሚያደርግበት መድረክ ማዘጋጀት እንዳለበት ተገልጸዋል፡፡

45 ይሁን እንጂ፤ባለስልጣኑ መ/ቤቱ ባዘጋጅው ዕቅድና አፈጻጸም መርሃ ግብር መሰረት አፈጻጸሙ ላይ በየደረጃው ግምገማ በማድረግ እና ወቅታዊ ጉዳዮችና በቀጣይ ትኩረት

---

[3] ከውል ስምምነት ውጭ መርከብ በባህር ወደብ ላይ የቆይታ ጊዜው በመራዘሙ ምክንያት የሚፈጠር ክፍያ

ተሰጥቷቸው ሊከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከአስመጪዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቋሚ በሆነ መልኩ ውይይት በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት የግምገማ ውጤት ግብረ-መልስ በጽሑፍ አዘጋጅቶ የማይላክ መሆኑን በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ ከግብርና ምርት ማሳደግያዎች አቅርቦት ዘርፍና ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቃለ መጠይቅ ለመወቅ ተችሏል፡፡

46 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ በየጊዜው ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ እና የቀጣይ አቅጣጫ የሚያሳይ መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት እያሰራጨ ሲሆን ለአብነት ለወደብ ኦፕሬሽን የተሰጠ አቅጣጫ በደብዳቤ ቁጥር ኮ/2/ማጉባ/781/07/08 መጋቢት 01 ቀን 2008 እና ለኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከግምገማው በመነሳት አቅጣጫ የተሰጠበት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/22/ማጉባ/898/07/08 መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ.ም ሲሆን በጥር 2008 ዓ.ም ደግሞ ሁሉም አጋር አካላት ያሳተፈ የድርጊት መርሃ-ግብር እና ሌሎችም በርካታ ማስረጃዎች በአባሪ መያዙን የበላይ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

47 የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ የሚፈላጉትን ማስረጃዎችን ባለስልጣኑ በደብዳቤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው መልስ ላይ በአባሪነት የተያዙ ከግምገማ ተነስተው የተሰጠ ግብረ-መልስ ሳይሆን በሌለ ጉዳይ ላይ የተጻጻፉት ደብዳቤዎች በመሆናቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

51 በዩኒሞዳል ትራንፖርት ሥርዓት የሚገቡ የከፍተኛ ብትን ጭነት ዕቅድ በአፈጻጸሙ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በየወቅቱ ስለማይደረግ ዕቃዎችን የያዙ መርከቦች በአንድ ጊዜ ያለፕሮግራም ተደራርበው በመምጣት በወደብ አንከሬጅ[4] ላይ እና መርከብ ማሽጊያ /በርዝ[5]/ ላይ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት ምክንያት ሆኖዋል፡፡

### የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማን በተመለከተ

52 ባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቀውን የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና መረሃ-ግብር መሠረት ለሚያስገቡ አስመጪዎች፣ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ

---

[4] መርከቦች ተራ ለማጠበቅ በባህር ላይ የሚሰፈፉበት አከባቢ

[5] መርከቦች ዕቃዎችን የሚያራግፉበት ቦታ

አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

53 የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በወጣው መመሪያ ላይ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መካከል አንዱ በጸደቀው ዕቅድ እና መርሃ-ግብር መሠረት ከፍተኛ የብትን ጭነቶችን ለሚያስገቡ አስመጪዎች እና የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እንዲሁም የመርከብ ወኪሎች ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና መስጠት እንዳለበት ተገልጾዋል፡፡

54 ይሁን እንጂ በብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና በመርሃ-ግብሩ መሠረት ከባህር ወደብ በወቅቱ ዕቃዎቻቸውን ወደ ሀገር ለሚያስገቡ አስመጪዎች፣ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተለይተው ተገቢው ግምገማ በማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና የማይሰጥ መሆኑን በናሙና ከተመረጡት አስመጪዎች ከኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅትና ከግብርና ምርት ማሳደግያና አቅርቦት ዘርፍ ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

55 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ ያለው ስንዴ፣ማደበሪያና ስኳር በመንግስት እንደሆነና የዚህንም የዕቃ አስተላላፊ ሥራ እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት በመሆኑም የፌደራል ዋና ኦዲተሮች የብትን ጭነት ዕቃ አሰተላላፊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመጠየቅ የሽልማት ሥርዓቱ አልተዘረጋም ለማለት የሚያስችላቸው አለመሆኑ እና የተባሉት የዕቃ አስተላላፊዎች እና አስመጪዎች በዚህ ዙሪያ የሚመለከታቸው አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

56 የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ ማስረጃዎቹ በአባሪነት ያልተያዙና በገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀት እና ለመቆጣጠር በወጣ መመሪያ መሠረት የከፍተኛ መጠን ጭነት አስመጪዎች የሚባሉት በአንድ ኦፕሬሽን ክብደታቸው 5000 ቶን እና ካዛ በላይ መጠን ያላቸው እንደ ድንጋይ ከሰል፣ስኳር፣ብረትና የመሳሰሉትን የሚያስገቡ ሲሆን በብትን ጭነት ደግሞ በመርከብ ተጓጉዘው መሬት ላይ ሳይራገፉ በወደብ ላይ ታሽገው በቀጥታ በመኪና ላይ በመጫን የሚጓጓዙ እንደ ማዳበሪያ እና የእርዳታ እህል መሆናቸውን የተገለጸ ቢሆንም ኃላፊው

የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ስንዴ አስመጪ፤የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት የድንጋይ ከሰል አስመጪ እና ግብርና ምርት ማሳደግያና አቅርቦት ዘርፍ የአፈር ማዳበሪያ አስመጪ ሆኖ ሳለ አይመለከታቸውም ማለት አግባብ ስላልሆነ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያደግታል፡፡

57 በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ በዕቅድ እና በመረሃ-ግብሩ መሠረት ስለመከናወኑ ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና ለድርጅቶቹ ስለመይሰጥ ያለድመሬጅና በወቅቱ ዕቃዎቻቸውን ለሚያስገቡ አስመጪዎች፤ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ለይተው እንድበረታቱ በማድረግ እና ሌሎችም አርያውን እንድከተሉ ማድረግ አልታቸለም፡፡

**የመረጃ ማዕከል ማደራጀትን በተመለከተ**

58 ባለስልጣኑ አሰፈላጊ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ማዕከል (on line data base) ሊያደራጅ ይገባል፡፡

59 በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በ2004 ዓ.ም ባጠናው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) የጥናት ሰነድ መሠረት ማንኛውም የሚመለከታቸው ድርጅቶች በቀላሉ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል (on line data base) በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይዘጋጃል የሚል ነበር፡፡

60 ነገር ግን በባለስልጣን መ/ቤቱ ደረጃ ከሚመለከታቸው የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃን በየዕለቱ ለማሰባሰብና በአንድ ማዕከል ለመያዝ የሚያስችል ዳታ ሲስተም (Data system) ባለመኖሩ አሰፈላጊና ወቅታዊ የሆኑ የሎጂስቲክስ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ ለማሳራጨት አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

61 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ዳታ ሲስተሙና የሎጂስቲክስ መረጃ ማዕከል ከ2006 እስከ 2007 ዓ.ም ለሙከራ ለዕቃ አስተላለፊዎች እንድጠቀሙበት የተሰረጨ ቢሆንም የተለያዩ ችግሮች ለመፍታት ሲባል በአሁኑ ወቅት በአዲስ መልክ መሠራት ላይ ያለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

62 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከወደብ ኦፕሬተሮች ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት የብትን ጭነት እና ሌሎችም ዕቃዎች መረጃ በየዕለቱ ለባለስልጣኑ እየተላከ ያለውን ወደ online data

system ለመቀየር የሚያስችል Mari-log የተባሉ ሶፍት ዌር ተሠርቶ በሙከራ ወቅት ችግር በማጋጠሙ ከብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት ጋር ጉዳዩን በመመካከር Web based እንዲሆን በተደረሰው ስምምነት ስራው በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወራሃዊ ሪፖርት በሀርድ ኮፒ እየተላከ ሪፖርቱንና የስምምነት ሰነዱን መመልከት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

63 በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ በማውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም መሠረት የተሟላ መረጃ እስከሚገኝ ድረስ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተጠናቀረ ዕለታዊ የወደብ መረጃ የሚሰባሰብበትና የሚሠረጭበት አሠራር ተግባራዊ መሆኑና በፊት ስሰራ የበነበረው ማሪ-ሎግ የተባለ ሶፍትዌር የነበረ ሲሆን የኢፌዲሪ ኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ሙያዊ ምክር ተጠይቆ (Web based) እንዲሆን የተወሰነ ቢሆንም ረዘም ያለ ጊዜ ቢወስድም አሁን የሙከራ ሂደት ላይ መሆኑን ቢገለጽም ሙከራ ስለመጀመሩን የቀረበው ማስረጃ በ2008 ዓ.ም ከኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ጋር ስለማሪ-ሎግ የሚባል ሶፍትዌር ለመፈተሸ የተጸጻፉት ደብዳቤ በመሆኑና መረጃን በየዕለቱ ለማሰባሰብና በአንድ ማዕከል ለመያዝ የሚያስችል ዳታ ሲስተም (Data system) እና የሚሠረጭበትም አሠራር ስለመኖሩ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

64 በመሆኑም በባለስልጣን መ/ቤቱ መረጃ ማዕከል (on line data base) ባለመደራጀቱና የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓቱንም በሀርድ ኮፒ በማድረጉ ምክንያት አሰፈላጊና ወቅታዊ የሆኑ የሎጂስቲክስ መረጃዎች **ለተጠቃሚዎች** በቀላሉ በማሰራጨት ጥቅም ላይ ማዋል አልተቻለውም፡፡

**በባህር ወደብ ላይ የቆዩ ገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ**

65 ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ ዕቃዎችን የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለይተው መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

66 በገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ ገጽ 7 ቁጥር 7.7 መሰረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መካከል ሀገራዊ የማሪታይም ሎጀስቲክስ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣

ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች የገቢ ዕቃዎችን መጠን በዕቃ ዓይነት በመለየት፣ በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ እንዲሁም በባህር ወደብ ላይ ስለተከማቹ ገቢ ዕቃዎች ከተለያዩ አካላት የሚላከውን መረጃ በወቅቱ መላኩን መከታተላል እና ማጠናቀር እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚገቡ የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ ማስረጃዎቹ ለመጠናቀርና ዕቃዎቹ የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለመለየት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

67 በዚሁ መመሪያ ገጽ 8 ቁጥር 8.1 መሰረት ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መካከል አንድ ዕቃ ከመድረሱ በፊት በሚያገኘው የመርከብ ጭነት መረጃ /Cargo Manfest/ መሰረት ትራንዚት በአግባቡ ያጠናቀቁና ያላጠናቀቁ የመከታተል እንዲሁም በየዕለቱ በወደብ የተራገፈው ገቢ ዕቃ ከተራገፈው ውስጥ የተነሳውን እና ያልተነሳውን የጭነት መረጃ የመያዝ ይህንኑ የወደብ መረጃ (Port Position) ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን እና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል የሚል ቢሆንም፣ በጉዳዩ ላይ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በበኩሉ በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አሁን ባለው አሰራር ከተለያዩ የመርከብ ወኪሎች የሚሰጥ ማኒፌስት የዩኒሞዳል እና የመልቲሞዳል ተጠቃልሎ የሚላክበት ሁኔታ በመኖሩና የሚጠቀሙበት የአሲኩዳ ሲስተም ከባለስልጣን መ/ቤቱ ሰርቨር ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ሲስተሙ የፖርት ፖዚሽን (port position) የማያወጣ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ መሰረታዊ የሆኑ በልክ ካርጎ ዕቃዎች ስንዴ፤የአፈር ማዳበሪያ፤ብረት፤ስኳር እና የኮንቴነር ብዛት በየቀኑ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የሚተላለፍ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68 ከዚህ በተጨማሪ በመመሪያው (የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ) ገጽ 8 ቁጥር 9.1 መሰረት የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መካከል አንዱ የድርጅቱ ንብረት በሆኑ መርከቦችና፣ በድርጅቱ ኃላፊነት በሌሎች የመርከብ ኩባንያዎች/ድርጅቶች/ የሚጓጓዝ የገቢ ዕቃዎች መረጃ በተሟላ መልኩ በማጠናቀር በየዕለቱ ለማታይም ጉዳይ ባለስልጣንና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መላክ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም፣ ስለጉዳዩ የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ

አገልግሎት ድርጅት በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የስንዴ፣ማዳበሪያና የስኳር ጭነቶችን የሚያሳውቁ መሆኑን፣ ከድርጅቱ መርከቦች ውጪ የሚጫኑ ሌሎች ዕቃዎችን ጨምሮ አጠቃላይ መረጃ ቢኖራቸውም የአስመጪዎችን ዝርዝርና የወደብ የቆይታ ጊዜን ግን ዝርዝር መረጃውን መስጠት እንደሚያስቸግራቸው ገልጸዋል፡፡

69 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በየዕለቱ ወደ ወደብ የሚደርሱ ዕቃዎች መረጃ የሚገኝበት ሥርዓት የተዘረጋና በየዕለቱም የሚገቡ ዕቃዎች መረጃ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከሁን ድረስ ያለውን ማየት የሚቻል መሆኑን ማስረጃውም በአባሪ መያዙን ገልጸዋል፡፡

70 ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በባህር ወደብ በየዕለቱ የሚደርሱ እና ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ ለባለስልጣኑ ይቀርባል የተባለው መረጃ ጥቂት የሆኑ የብትን ጭነቶችና መቼ እንደገቡ በትክክል የማይታወቁ የከሰል ድንጋይ፣ ስንዴ፣ ባለቤቱ የማይታወቅ ኮንቴይነሮች ከመሆኑ በተጨማሪ መረጃውን በመተንተን ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ ማቅረብ ያልተቻለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

71 በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ከባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት እና ባለስልጣን መ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በጻፈው ደብዳቤ መሠረት ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ ዕቃዎችን የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት እንዲችል የተሟላ ማስረጃ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባላገኘበት ሁኔታ ለመስራት አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72 በባለስልጣን መ/ቤቱ በባህር ወደብ ላይ ከ8 ቀናት በላይ የቆዩ ገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ ችግሮቻቸውን ለይተው መፍትሄ ባለመስጠቱ ምክንያት ሀገሪቷ መጠኑ ያልተወቀና አግባብ ያልሆነ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ተደርጋለች፡፡

**የዲመሬጅ ክፍያ መረጃ አያያዝን በተመለከተ**

73 ሀገሪቱ በየዓመቱ ወጪ የሚታደርገውን የዲመሬጅ ክፍያን በተመለከተ ባለስልጣኑ በዝርዝር መረጃዎችን በመከታተልና በማሰበሰብ በየዓመቱ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

74 ነገር ግን ይህ ስለመከናወኑ በኦዲቱ ወቅት የቀረበ መረጃ በተከለሰበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል ፡-

- በሀገሪቷ በየዓመቱ በዲመሬጅ ምክንያት ወጪ የምታደርገውን የውጭ ምንዛሪ ክፍያን በተመለከተ በአጠቃላይም ሆነ በዝርዝር መረጃው ባለስልጣኑን ጨምሮ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልሰልጣን እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማይያዝ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በተጨማሪም መረጃው በባለስልጣኑ ባይያዝም በጅቡቲ የሚገኝ በኢትዮጵያ በ ገቢዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሙሉ መረጃ እንደሚያዝ የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በቃል-መጠይቅ የገለጹ ቢሆንም በጅቡቲ የገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በጂቡቲ በተደረገው መስክ ጉብኝት ወቅት በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በስጡት መልስ የዲመሬጅ ክፍያ በተበታተነ መልኩ በአስመጪዎች አማካይነት የሚፈጸምና የመ/ቤታቸው ኃላፊነት ባለመሆኑ፣ሥራው የማሪይታም ጉዳይ ባለስልጣን በኩል መፈጸም የሚገባ ተግባር ስለሆነ መረጃው በጅቡቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩልም የማይያዝ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

75 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለወደብ የሚከፈለው ክፍያ እና አጠቃላይ ወጪ ለማስላት የሚያስችል የዳሰሳ ሥራ ተሰርቶ አመላካች የሆኑ ቁጥር የተገኘ ቢሆንም፤ ይህን በዘላቂ ሥርዓት በየአመቱ እየተጠና በየሴክተሩ እና በየዕቃው ዓይነት ለመለየት ተቋሙ ካለበት የሠው ሃይል እጥረት አንጻር የልተሠራ ሥራ እንደሆነ ተገልጸዋል፡፡

**ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ**

76 ባለስልጣን መ/ቤቱ ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር (ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፤ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች) በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን መጠን፤ ዓይነት፤ የቆይታ ጊዜ እና በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት መረጃዎቹን ሊያጠናቅር ይገባል፡፡

77 በገቢ ዕቃዎች ትራንዚትና ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ መሠረት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መካከል ፣ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣ከኢትዮጵያ

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች የገቢ ዕቃዎችን መጠን፣ በዕቃ ዓይነት በመለየት፣ በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ እንዲሁም በባህር ወደብ ላይ ስለተከማቹ ገቢ ዕቃዎች ከተለያዩ አካላት የሚላከውን መረጃ በወቅቱ መላኩን ይከታተላል ያጠናቅራል የሚል ነው፡፡

78 ይሁን እንጂ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሀገራዊ የሆነ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በተመለከተ በኢ-ሜይል በየቀኑ ከተለያዩ ዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች ለባለስልጣኑ ሲላክ የነበረው በ2006 ዓ.ም መ/ቤቱ ሥራ ላይ አውሎት የነበረ ሶፍትዌር የገቢና ወጪ ዕቃዎችን ኦፕሬሽን ሙሉ መረጃ ከዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች ተቀብሎ እና አጠናቅሮ ለባለስልጣኑ የሚያሳውቅ የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ተዘርግተው የነበረ ቢሆንም ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራው ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ መሆኑን በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

79 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ Mari-Log Software ተሠርቶ ሙከራ ላይ የነበረ ሲሆን በሙከራ ወቅት ቴክኒካል ችግር በማጋጠሙ ዌብ ቤዝድ አድርጎ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ሲሆን ቀደም ሲል ለባለስልጣኑ ሊላኩ የነበሩ መረጃዎች በሀርድ ኮፒ በየወሩ ከዕቃ አስተላላፊዎች እንደሚሰበሰብና ማስረጃዎቹን በአባሪ መያዙን ገልጸዋል፡፡

80 ባለስልጣን መ/ቤቱ ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር ባለመዘርጋቱና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ ባለመጠናከሩ ምክንያት በባህር ወደብ ላይ ሰለተከማቹ ገቢ ዕቃዎች ሁኔታ፣ትክክለኛው የቆይታ ጊዜ እና በኦፕሬሽን ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ላይተው ለማወቅና ወቅታዊ እርምጃ ለማውሰድ አልተቻለም፡፡

**ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ**

81 ባለስልጣን መ/ቤቱ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረገ አካልን በመከታተልና መረጃ በመሰብሰብ ተጠያቂ የሚሆኑበት የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡

82 የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር በወጣው መመሪያ ላይ በክፍል ሁለት ገጽ 20 ቁጥር 6 ንዑስ ቁጥር 6.15 ላይ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መካከል አንዱ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን

ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረገ አካልን ተጠያቂ የሚያደርግ የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ያቀርበል የሚል ነው፡፡

83 ባለስልጣን መ/ቤቱ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች፣ዕቃ አስተላለፊዎች፣መርከብ ወክሎችና ሌሎች አካላትን መረጃ አጠናቅሮ የማይያዝና ድርጅቶችን ተጠያቂ የሚያደርግበት የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

84 በተጨማሪም የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ዝርዝር መረጃዎች በጅቡቲ የገቢዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንደሚገኝ የተገለጸ ቢሆንም፣ የኦዲት ቡድኑ በጅቡቲ ባካሄደው የመስክ ጉብኝት ወቅት ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው የዲመሬጅ ክፍያ በተበታተነ መልኩ በአስመጪዎች አማካይነት የሚፈጸም በመሆኑና የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊነት ባለመሆኑ ከወደብ አጠቃቀም አኳያ በማሪታይም ባለስልጣን በኩል መፈጸም የሚገባ ተግባር መሆኑን የሥራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

85 ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በወደቦች ውስጥ ያለአግባብ የሚከማቸውን ዕቃ መጠን ለመቀነስ እና አስመጪዎችን ለመደገፍ፣ ከዚያም እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ መመሪያዎች ውስጥ በባህር ወደብ ላይ የተተው እቃዎች መመሪያ፣እቃዎችን በደረቅ ወደብ ስለማስቀመጥና ማውጣት የመሳሰሉት መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

86 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የተጠቀሰው ጉዳይ በኦዲት ወቅት ጥያቄው ቀርቦ ለማብራራት የተሞከረ ቢሆንም ዲመሬጅን በተመለከተ በባለስልጣኑ ሁለት ጊዜ ተጠንቶ ለመንግሥት የቀረበ ሲሆን ዲመሬጅን በየዕለቱ አጠናቅሮ ለመያዝ ከፍተኛ ሪሶርስ እና የሠው ሃይል የሚጠይቅ ከመሆኑም አንጻር በየዓመቱ መሠረት እንደለበት ታምኖበት ኮሚቴ ተቋቁሞ በ20/03/14 በ2015/16 ሁለት ጥናቶች ተጠንተው ለትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ለሚመለከታቸው የቀረበ መሆኑና የጥናቶቹም ቅጅ አባሪ እንደተደረገ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

87 በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት የተጠቀሱትና በአባሪነት ቀርቧል የተባሉት ጥናቶች በ2006 ዓ.ም የከፍተኛ መጠን ገቢ ጭነት አገባብ ኦፕሬሽናል ዕቅድ በሚል በተዘጋጀ ዶክሜንቶች መሠረት የስቶሬጅና ተዛማጅ የወደብ ክፍያዎችን በተመለከተ እ.አ.አ

ከጥር 2012 እስከ ሰኔ 2013 የከፍተኛ መጠን ጭነት ብቻ 38,522,598.11 የአሜሪካን ዶላር የተከፈለ ሲሆን የፕሮጅክት ካርጎ ደግሞ 4,120,246.10 በድምሩ 42,642,844.21 የአሜሪካን ዶላር ነው:: (ዝርዝሩ በአባሪ-4 ተያይዟል) ፡፡

88 በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የ2006 ዓ.ም ጥናት ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላት ሪፖርት ተደርጓል በሚል ማስረጃዎቹን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በጻፈው ደባዳቤ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች በጥር ወር 2009 ዓ.ም የ2016 እ.ኤ.አ የብትን ጭነት አገባብ በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት በሚል ለትራንስፖርት ሚኒስቴር የተለከ ደብዳቤና አባሪ የተደረገ ሲሆን የተጠየቀው ግን የ2006 ዓ.ም በመሆኑና በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች ተጠያቂነት ለመዘርጋት ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሙሉ መረጃው ስላልተገኘ ነው ቢሉም ሙሉ መረጃዎችን የሚያገኝበት አሰራር መዘርጋት ያለበት ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

89 በ2008 ዓ.ም የደረቅ ብትን ጭነት ሎጅስቲክስ ፕሮግራም በሚል በተጠና ደግሞ የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት ለመርከብ ዲመሬጅ ብቻ በበጀት አመቱ ዝቅተኛ ስሌት ቢያንስ 5.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በአጠቃለይ የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት የሎጅስቲክስ ወጪ ዓመታዊ አማካኝ 257.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይም 5.6 ቢሊዮን ብር ሲሆን በዩኒሞዳል በሚጓጓዙ የጀነራል ካርጎ ጭነት ላይ የብትን ጭነት ኦፕሬሽን ባስከተለው ጫና ለተጨማሪ ብር 162.1 ሚሊዮን ወጪ የወጣ ሲሆን በድምሩ 5.76 ቢሊዮን ብር አላግባብ ወጪ መሆኑን ያስረዳል፡፡

90 የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ የ2008 ዓ.ም የተካሄደውም ጥናት በጥቅል የቀረበና አላግባብ የወጣውን ወጪ በማን እንደሆነ ዝርዝር መረጃ ያልያዘ በመሆኑና በባለስልጣን መ/ቤቱ ጉዳዩ እየታወቀ የሁለቱንም ዓመታት በወቅቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላት ሪፖርት ስለማድረጉ ማስረጃ ያልቀረበና ጉዳዩን በተመለከተ በሀገር ደረጃ አሳሳቢ መሆኑን ግንዘቤ ውስጥ በማስገባት ባለስልጣኑ ትኩረት ሰጥተው በቀጣይነት በየዓመቱ ማጥናትና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ ሲገባው ባለመድረጉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

91 በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ በማውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የ2008 ዓ.ም ጥናት ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላት ሪፖርት ተደርጓል በሚል ማስረጃዎቹን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች በ2008 ዓ.ም የደረቅ ብትን ጭነት ሎጅስቲክስ ፕሮግራም ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ስለመላኩ የተጻፈ ደብዳቤ ሲሆን የደብዳቤውም ቁጥር ኮ/43/ማጉባ/1366/11/08 በቀን 20/11/08 ዓ.ም የተጻፈ ሲሆን ጥናቱ የተጠናቀቀው ግን ነሐሴ 2008 ዓ.ም ስለሆነ ጥናቱ ሳያልቅ ደብዳቤው ቀድሞ መጻፉን የሚያሳይ በመሆኑና የሚመለከታው የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ፊርማ ሆነ የተቋሙም ማህተም የሌለ በመሆኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጠን ማስረጃ ትክክለኝነቱ ጥያቁ ውስጥ የሚገባ ስለሆነ የቀረበውን ማስረጃ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

92 ይህ ባለመሆኑ ሀገሪቷ በያዓመቱ በዲመሬጅ ምክንያት አግባብ ባልሆነ መልኩ የሚታጣውን የውጭ ምንዛሪን ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን ለጨመር ይችላል፡፡

**እቃዎቻቸውን በወቅቱ የማያነሱ አስመጪዎች ላይ የእርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ**

85 ባለስልጣን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ድጋፍ ተደርጎላቸው በባህር ወደብ ላይ እቃዎችን በ30 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ በየወቅቱ በማጠናከር እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት በማድረግና በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

86 በገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ መሠረት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት፤ በተደጋጋሚ ድጋፍ ተደርጎላቸው በባህር ወደብ ላይ ዕቃቸውን በ30 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ በማጠናቀር እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል የሚል ነው፡፡

- ይሁን እንጂ ይህ ስለመከናወኑ በኦዲቱ ወቅት የቀረበ **መረጃ በተከለሰበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል** ፡-በባህር ወደብ ላይ በወቅቱ የማይነሱ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ የከፍተኛ መጠን ጭነት የሆኑ ገቢ ዕቃዎች (ከሰል ድንጋይ፣ስኳር፣ብረትና ስንዴ እና የተለያዩ ኮንንቴነሮች) ለባለስልጣን መ/ቤቱ በባህር ወደብ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ሪፖርት የሚቀርብ (port position) ቢሆንም ሪፖርቱ በትክክል ዕቃዎቹ በዝርዝር መቼ

እንደተራጋፉና ከባህር ወደብ እንደተነሱ፤ በወደብ ላይ የቆዩበት ትክክለኛ የሆነ ቀናት የማያሳይ እና እርምጃም እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በ30 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ ሙሉ ዝርዝር በጅቡቲ የሚገኝ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንደሚያዝ የገለጹ ቢሆንም ኦዲት ቡድኑ በጂቡቲ በካሄደው መስክ ጉብኝት ወቅት የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በስጡት መልስ የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ተግባር ባለመሆኑ መረጃው እንደማይያዝ ገልጸዋል፡፡

87 ይህንን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ መረጃዎቹ ተጠናቅረዋል፤ለሚመለከተው አካል እንደሚተላለፍ ገልጸዋል፡፡

88 የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ በቃለ መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በባህር ወደብ ላይ ያለበቂ ምክንያት እቃዎችን የማያነሱ አስመጪዎችን ዝርዝር መረጃ እና እርምጃ እንዲወሰዲባቸው ምንም ሪፖርት ያልቀረበላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

89 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማውጫ ስብሰባ ወቅት ማስረጃዎችን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በተጻፈው መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች በዩኒሞዳል የገቡ ዕቃዎች በጅቡቲ ወደብ ከእፎያታ ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ ዕቃዎችውን የማያነሱ አስመጪዎችን ሪፖርት ለቤሄራዊ ባንክ ለውሳኔ የመላክ ኃላፊነት ባለስልጣኑ ቢኖርበትም ትክክለኛና የተሟላ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ አስመጪዎችን ተጠያቂ ማድረግ ተገቢ አይደለም ቢሉም ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃውን የሚቀበልበት ሥርዓት መዘርጋት ሲጋባው ማስረጃዎቹ የሉም ማለት አግባብ ስላልሆነ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

90 ይህ ባለመሆኑ በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ ለመተንተን በሚያመች መልኩ በመጠናቀር እና በተገቢው ጊዜ ዕቃዎቻቸውን ከባህር ወደብ የማያነሱ አስመጪዎች ተገቢውን ድጋፍም ሆነ ማስተካከያ እርምጃ እንደይወሰድ አድርጓል፡፡

**በባህር ወደብ ላይ የተተው ዕቃዎችን በተመለከተ**

91 ባለስልጣን መ/ቤቱ የተተዉ እቃዎች በወቅቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት በጊዜው ማሳወቅ እና እቃዎቹ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

92 በጅቡቲ ወደብ ላይ የቆይታ ጊዜያቸው ያለፈ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በአስመጪዎቻቸው ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ወይም የሚወገዱበትን አኳኋን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 33/2005 ላይ ለማሪይታም ጉዳይ ባለስልጣን የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አንዱ ከኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በሚቀርብለት ሪፖርት የመመሪያውን አፈጻጸም ይከታተላል፤ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደሚመካከር ተጠቅሷል፡፡

93 በተጨማሪም ለሎጂስቲክስ ማስተባበሪያ እና ክትትል ዳይሬክተር በተሰጡት የሥራ መዘርዝር መሠረት በባህር ወደብ የተተው ዕቃዎችን መረጃ በወቅቱ ተከታትሎ ማስተላለፍ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ እንዳለበት ተገልጾዋል፡፡

94 ይሁን እንጂ በባህር ወደብ ላይ የተተዉ እቃዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎችን ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ግማሽ ዓመት የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከ2006 እስከ 2007 ዓ.ም ብቻ ያልተሟላ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያቀረቡ ሲሆን የተሰበሰበው መረጃ ሙሉና ወቅታዊ ባለመሆኑ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ ተተንትኖ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሪፖርት አለመደረጉ እና ከ2008 እስከ 2009 ዓ.ም ያለው መረጃ ግን ያልተሰበሰበና ለሚመለከታቸው አካላትም እንዳልቀረበ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

95 በተጨማሪም የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ሙሉ መረጃውን በተመለከተ በጅቡቲ የሚገኝ በገቢዎችና ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንደሚያዝ የገለጹ ቢሆንም ኦዲት ቡድኑ በጂቡቲ በካሄደው መስክ ጉብኝት ወቅት የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በስጡት መልስ በባህር ወደብ የቀሩ ዕቃዎች በሁለቱም ሀገሮች መካከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት ስልጣን የተሰጠው የማሪታይም ባለስልጣን በመሆኑ ትራንዚት ተፈቅዶ ሲመጣ ከማስተናገድ ውጪ የሚሰራ ስራ አለመኖሩን ገልጾዋል፡፡

96 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ መረጃውን በተመለከተ  በወቅቱ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም የተባለው ፈጽሞ ትክክል እንዳልሆነ እና እ.አ.አ ከ2009-2016 ያለውን አሁንም ድረስ መረጃው በእጃቸው ያለ በመሆኑም ምንአልባትም ኦፕሬሽኑን እና የመረጃዎችን ምንነት ካለመገንዘብ የመጣ ከሆነ በቀጣይም  ተነጋግሮ እንደሚፈቱና በአባሪ ማስረጃው መያዙን ገልጸዋል፡፡

97 የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለኦዲት ቡድኑ ቀርቧል የተባለውና በአባሪነትም የቀረበውም ማስረጃ እ.አ.አ ከ2010 እስከ 2015 ብቻ ሲሆን ቀሪው የሁለት ዓመት ከ2016-2017 ያልቀረቡና በሪፖርትም ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ትንተና ተሰርቶ ስለመላኩ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መለስ ለመቀበል አያስችልም፡፡

98 በተጨማሪም የተተው እቃዎችን በተመለከተ በማውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ ቀሪው የሁለት ዓመት የ2016-2017 ያልቀረቡና በሪፖርትም ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ትንተና ተሰርቶ ስለመላኩ የሚያሳይ ማስረጃዎችን  አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በተጻፈው መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች የ2015 በባህር ወደብ ላይ የተተው የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ ወደ ሀገር እንደልገቡ በመጥቀስ የ2016-2017 ያለውን ዝርዝር ማስረጃዎችን መቅረብ አለመቻሉን ባለስልጣን መ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡

99 ይህ በመሆኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተተዉ እቃዎች በወቅቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ባለማሳወቁ ምክንያት በባህር ወደብ የተተው ዕቃዎች ሳይበላሹና ተጨማሪ ወጪ በሀገር ላይ ሳያስከትሉ ማንሳት አልተቻለም፡፡

**የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነትን በተመለከተ**

100 ባለስልጣን መ/ቤቱ የገቢ ዕቃዎች እና የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) የትራንዚት ትራንፖርትን በተመለከተ ባበህር ወደብ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር፤ ምክክር እና የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት በማድረግ ሊከታተልና ሊያሻሽል ይገባል፡፡

101 በ1994 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 284/94 የጸደቀው የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት

ስምምነት፣በክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት ሁለቱም ሀገራት ካርጎ/ዕቃ በባህር ወደብ ከተረጋፈ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ቀናት ብቻ ለገቢ ዕቃዎች ያለምንም ክፍያ /30 days are Grace period for Import Transit Cargo/ በባህር ወደብ መቆየት እንደሚቻል ተቀምጧል፤

102 ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሻሻያ ያልተደረገ እና የገቢ ዕቃዎች ያለክፍያ በባህር ወደብ መቆየት የሚችሉት ወይም የእፎይታ ጊዜ እስከ 8 ቀናት (8 days are Grace period for Import Transit Cargo) በመሆኑ አገሪቷ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ ለቆዩ ዕቃዎች ዲመሬጅ እየከፈለች መሆኑ፤

103 ይህንን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሁለቱ ሀገራት በፈረሙት ስምምነት መሠረት  የገቢ ዕቃ በባህር ወደብ ቆይታ ለ180 ቀናት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 30 ቀናቱ ክፍያ የማይከፈልበት መሆኑ ነው የተገለጸው፤ አሁን በተግባር የሚታየው አሠራር ከስምምነቱ ማዕቀፍ ውጭ የሆነ ሲሆን ሊሆን የቻለበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት የማይችሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

104 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 549/99 የተቋቋመው በ1999 ዓ.ም ነሐሴ ወር ሲሆን በ2000 ዓ.ም የመደራጀት ሥራ ተሠርቶ በ2001 ዓ.ም በአንድ ሰው ሥራ የጀመረ በመሆኑ በጅቡቲ ወደብ የታሪፍ ማሻሻያ ፕሮፖዛል ለኢትዮጵያ መንግሥስት የቀረበው ደግሞ እ.አ.አ June 24-2008 (በ2000 ዓ.ም) ሲሆን ጉዳዩንም ስከታታል የነበረው በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በንግድ ሚኒስቴር ለወደብ አጠቃቀምና ትራንዚት ጉዳይ በማሳወቅ ንግድ ሚኒስቴር ኮሚቴ አቋቁሞ ጉዳዩን በዝርዝር አስጠንቶ ለመንግሥት ያቀረበ ሲሆን በወቅቱ ምላሽ ባለመሰጠቱ ወይም በጅቡቲ በኩል ተግባራዊ ስለሆነ ታሪፉ ተቀባይነት አግኝተው ሊሆን እንደሚችልና ጉዳዩም በላስልጣኑን የሚመለከት አለመሆኑን ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

105 የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ መንግሥት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን  በአዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት ከተሰጠው ተግባርና ሥልጣን ውስጥ አንድ የባህር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚከሰቱ ችግሮች ተከታትሎ መፍትሔ መስጠት፣ መደራደር፣ እና ትራንስፖርት ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል የሚል በመሆኑ ባለስልጣኑ

ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ይህን ሥራ መስራት ሲጋባው አይመለከተኝም ማለቱ አግበብ ስላልሆን የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

106 በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት ለባለስልጣኑ ከተሰጡት ተግባርና ሥልጣን ውስጥ ፤የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ መምራት፣ የባህር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚከሰቱ ችግሮች ተከታትሎ መፍትሔ መስጠት፣ መደራደር፣ እና ትራንስፖርት ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል የሚል ነው፡፡

107 በአዋጅ ቁጥር 284/94 የጸደቀው የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት ሁለቱም ሀገራት ካርጎ/ዕቃ በባህር ወደብ ከተረጋፈ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ቀናት ብቻ ለገቢ ዕቃዎች ያለምንም ክፍያ /30 days are Grace period for Import Transit Cargo/ በባህር ወደብ መቆየት እንደሚቻል የተደነገገ በመሆኑ አሁን እየተተገበረ ያለው የጅቡቲ ባህር ወደብ ታሪፍ ገቢ ዕቃዎች/ ካርጎ በባህር ወደብ ላይ መቆየት የሚቻለው እስከ 8 ቀናት የእፎይታ ጊዜ /8 days are Grace period for import Cargo/ ብቻ በመሆኑ ሀገሪቷ ይህን የእፎይታ ጊዜ የተቀበለችበት የህግ አግባብ ወይም በሁለቱም ሀገራት መከካል የተሻሻለ የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት ስለመኖሩ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

108 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በስምምነቱ ላይ እንደተገለጸው ስምምነቱ ማሻሻል ሲያስፈልግ ሥርዓቱ በጠበቀ መልክ መሆን እንደለበት ቢጠቀስም በባህር ወደብ ላይ ገቢ ዕቃዎች ለ8 ቀናት ብቻ ያለክፍያ መቆየት የሚለው ግን ሕጋዊ ማስረጃ አለው ብሎ የማያምኑ መሆናቸውን አብራርቷል፡፡

109 በተጨማሪም የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሻሻያን በተመለከተ በማውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃዎችን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በተጻፈው መሠረት የእፎይታ ጊዜው ለውጥ የተደረገው በ2000 ዓ.ም ሲሆን ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ሥራ የጀመረው በአንድ ሠው በ2001 ዓ.ም ስለሆነ ጉዳዩን ክትትል ሲያደረግ የነበረው

የቀድሞ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመሆኑ ቢገለጽም በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የባህር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ የመደራደር ስልጣን የተሰጠው ለባለስልጣኑ መ/ቤት በመሆኑና የተጠየቀውም በባለስልጣን መ/ቤቱ የህግ አግባብ እንዲኖረው የተሠራ ስራና በሁለቱም ሀገራት መከካል የተሻሻለ የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት ስለሆነ የቀረቡ ማስረጃዎች ለመቀበል ያዳግታል፡፡

110 በጅቡቲ ባህር ወደብ የወደብ አገልግሎትን በተመለከተ የማራገፍ፣የመጫን፣የመቋጠርና የመጋዘን አገልግሎት ውል ስምምነት/Stevedoring Services Agreement በሚል በኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት/ Ethiopian petroleum Enterprise እና የPort Autonome International Djibouti ጋር በ2004 ዓ.ም ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን እውቅና ውጭ የተፈራረመና ተግባራዊ እየሆነ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

111 ጉዳዩን በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በባለስልጣኑ እውቅና ውጭ የባህር ወደብን በተመለከተ ሌሎች ድርጅቶች የውል ስምምነት ማድረግ ጋር በተያየዘ በማሪታይም አዋጅ ላይ እንደተጠቀሰው ባለስልጣኑ ወደብን በተመለከተ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ጠበቂነት መደራደር የሚችል ብቻኛ ተቋም ነው፡፡ ይህ ከባለስልጣን መ/ቤቱ እገዛና ዕውቅና ውጭ ተፈረመ የተበለው ስምምነት በምን ምክንያት እንደተፈረመ የማያውቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

112 ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በጅቡቲ ወደብ የብትን ደረቅ ጭነትን የስቴቨደሪንግ አገልግሎት የሚሰጠው SDTV ሲሆን ይህ ድርጅት ውል የሚዋዋለው ከአስመጪዎች (ከማደበሪያ አቅራቢ ድርጅት፣ከስንዴ አስመጪ ድርጅትና ከስኳር አስመጪ ድርጅት) ሲሆን የነዳጅ ደግሞ የስቴቨደሪንግ አገልግሎት የሚሰጠው PAID የሚበል ድርጅት ከነዳጅ አስመጪው ጋር ቢዋዋል ምንም አይነት ክፈተት እና ጉድለት አለመኖሩን ጠቀሰው የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወደብ ድረስ ሂደው ድርድሩን ከጨረሱ በኃላ ስምምነት መፈጸም የሚችል ግን ነዳጅ ድርጅት በመሆኑ ፊርማ ያልፈረሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

113 በተጨማሪም የባህር ወደብ አገልግሎትን በተመለከተ በማውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረጃዎችን አቀርባለው ባለው መሠረት በደብዳቤ ቁጥር ኮ/1/ማጉባ/1223/08/09 በቀን 05/08/2009 ዓ.ም በተጻፈው መሠረት ደግሞ

የማራገፍ፣የመጫን፣የመቋጠርና የመጋዘን አገልግሎት ውል ስምምነት/Stevedoring Services Agreement/ ድርድርን በተመለከተ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የኃላፊነት መሆኑን አምኖ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

114 የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ አስመጪዎቹ ከአገልግሎት ሰጪ አካላት ጋር ውል ስምምነት ከማድረጋቸው አስቀድሞ ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከወደብ ባለቤቶቹ/ አገልግሎት ሰጪዎቹ ጋር ድርድር በማድረግ ከአስመጪዎቹ ጋር እንድዋዋሉ ስለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን አስመጪዎቹ ለየብቻቸው መደራደር እና ውል ማድረግ በሀገር ደረጃ ወጥ ያልሆነ አሰራር ከመሆኑም በላይ አግባብ ያልሆነ ክፍያ ሀገሪቷን ሊያደርግ ስለሚችል የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አያስችልም፡፡

115 ይህ በመሆኑ ሀገሪቷ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ያጸደቀችሁን የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም ስምምነት ውጭ በጅቡቲ የተዘጋጀውን የባህር ወደብ ታሪፍ ስታንደርድ መሠረት ብቻ ባለስልጣኑ በስምምነቱ ላይ ድርድር በማድረግ በሀገሪቱ ደረጃ በማሻሻል የህግ መሠረት ወይም የህግ አግባብ እንድኖረው ማድረግ ሲገባው በባህር ወደብ ላይ ያለ ክፍያ ገቢ ዕቃዎች ከ30 ቀናት ወደ 8 ቀናት ያለስምምነት እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ሀገሪቱ 22 ቀናት ያለአግባብ ለገቢ ዕቃዎች ከፍተኛ የሆነ ወጪ በየዓመቱ እየከፈለችና አስመጪዎች ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ በባህር ወደብ ላይ እቃዎቻቸውን ያቆዩትን ተጠያቂ ለማድረግ የህግ ክፍታት እንድኖር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

## ክፍል ሦስት

### መደምደሚያ

በናሙና ተመርጠው በታዩ የአስመጪዎች፣ዕቃ አስተላላፊዎች እና ተቆጣጣሪ አካላትን በተመለከተ የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

116 በብሄራዊ ደረጃ በየበጀት ዓመቱ የሚዘጋጅ የከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድና መርሃ-ግብር የሁሉም ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት በዳሰሳ ጥናት በመለየት እና በዝርዝር የሃላፊነታቸውን በግልጽ በማስቀመጥ፣ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ውይይትና ምክክር በማድረግ ስምምነት ላይ በማድረስ ዕቅዱ እያዘጋጅ ስለልሆነና በሚያስፈልግበትም ጊዜም ዕቅዱን ስለማይከለስ ትክክለኛ የሆነ የከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድና መርሃ-ግብር ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡

117 በባለስልጣን መ/ቤቱ ተዘጋጅቷል የተባለው የከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና መርሃ ግብር ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ሁሉ የማይደርስ ከመሆኑም በሻገር በአፈጻጸሙ ላይ በተቀመጠው አመታዊ ፕሮግራም መሰረት መሆኑን አፈጻጸሙን ከዕቅድ ጋር ንጽጽር ተደርጎ ግምገማ እየተደረገ በለመሆኑ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ወደ ሀገር እየገቡ ያሉ ገቢ ዕቃዎች ላይ ባለስልጣኑ በአግበቡ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አልተቻለውም፡፡

118 በጸደቀው አመታዊ ዕቅድና መርሃ-ግብር መሰረት ለሚያስገቡ አስመጪዎች፣ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎችን ለማበረታታት በየጊዜው ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና ስለማይሰጥ፣ በተቀመጠው መመሪያና በተዘጋጀው እቅድ መሰረት እቃዎቻቸውን የማያስገቡና በወቅቱ እቃዎቻቸውን ከባህር ወደብ የማያነሱ አካላትን ባለስልጣኑ የመለየት ሥራ መስራት አልቻለም፡፡

119 በሀገር ደረጃ ከጸደቀው መርሃ-ግብር ውጪ የሚያስመጡና በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃዎቻቸውን ከባህር ወደብ የማያነሱ አስመጪዎች ተለይተው ማስረጃው ስለማይያዝ ሀገሪቱን ለማይገባ የውጭ ምንዛሪ እንዲትዳረግ ከመደረጉ በላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅቶቹን ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድባቸው/ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ አልቻለም፡፡

120 በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች፣ዕቃ አስተላለፊዎችና የመርከብ ወክሎች በተመለከተ መረጃዎቹ

በባለስልጣን መ/ቤቱ ተለይተው በየጊዜው ስለማይሰበሰብና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላትም ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሪፖርት ማቅረብ ባለመቻሉ ሀገሪቱ በየዓመቱ ያልተፈለገ በውል ያልተወቀ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ እንድትዳረግ እያደረገ ነው፡፡

121 በባህር ወደብ ላይ ከ8 ቀናት በላይ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ (የዕቃው ባለቤት፣የዕቃው አይነት፣መጠን፣የቆይታ ጊዜና የቆዩበት ምክንያት) በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚለይበት አሰራር ሥርዓት ባለመኖሩ በወደብ ላይ ያለው ገቢ ዕቀዎችን ተለተው ለማወቅና ለቆዩበት ምክንት መፍተሄ መስጠት ለባለስልጣኑ አልተቻለውም፡፡

122 በዩኒሞዳል ሥርዓት የሚገቡ ዕቃዎቹ በባህር ወደብ ላይ ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ በመቆየታቸው ሀገሪቷ በዲመሬጅ ምክንያት በየዓመቱ የሚታጣውን የውጭ ምንዛሪ ክፍያ በአጠቃላይም ሆነ በዝርዝር መረጃዎቹ በሌሎችም የመንግሥት መ/ቤቶችም በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልሰልጣን እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ስለማይያዝ በሀገር ደረጃ ውሳኔ መስጠት ለሚችል ለመንግሥት አካል ጉዳዩ ቀርቦ መፍተሄ ማግኘት አልቻለም፡፡

123 ሀገራዊ የሆነ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለመደገፉና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋርም ቅንጅታዊና ቀጣይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ባለመዘርጋቱ በየዕለቱ በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ (የዕቃው ባለቤት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ የገባበትና የወጣበት ጊዜ ፣ በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን) ለመለየትና ወቅታዊ የሆነ መረጃ መያዝ ለባለስልጣኑ አልታቸለም፡፡

124 በዩኒሞዳል የገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ በባህር ወደብ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ እቃዎቻቸውን የማያነሱ አስመጪዎች ከሚመለከታቸው አካላት መረጃውን በየወቅቱ ተሰበሰብው ስለማይደራጅ አስመጪዎቹን መለየትና ተገቢ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ አስቻገሪ አድርጎታል፡፡

125 በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል በባህር ወደብ ላይ የተተዉ እቃዎችን ሁኔታ በቅድሚያ ተለይተው ዝርዝር መረጃዎችን ተሰበሰብው ስለማይጠናቀርና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ተደርገው በወቅቱ ወደ ሀገር እንድገቡ ስለመይደረጉ እቃዎቹ ለተለያየ ብልሽትና ሀገሪቷን አግባብ ያልሆነ የውጭ ምንዛሪ ወጪ እየተዳረገች ትገኛለች፡፡

126 ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነቶችን በባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪዎች የዕቃ አስተላላፊ፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን፣ በአገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበትን የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት በየጊዜው ስለማይሰበሰብና ክትትልና ቁጥጥር ስለማይደረግ ለመርከብ መደራረብና ለመኪና እጥረት እንድትዳረግ ምክንያት ሆኖዋል፡፡

127 ሀገሪቷ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ያጸደቀችሁን የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም ስምምነት ሳይሻሻል እና ከባለወደቡ ጋር ድርድር በለመደረጉ ሀገሪቷ አግባብ ባለሆነ መንገድ የገቢ ዕቃዎች ያለክፍያ በባህር ወደብ መቆየት የሚችሉት ወይም የእፎይታ ጊዜ አጭር በመሆኑ ለከፍተኛ ወጪ እየተደረገች ትገኛለች፡፡

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን በዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ አፈጻጸም ላይ የታዩትን ጉድለቶችን ለማስወገድ ወይም ለማስተካከል ይረዳሉ ብለን ያስብናቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

128 ባለስልጣን መ/ቤቱ በብሄራዊ ደረጃ በየበጀት ዓመቱ የሚያዘጋጅው የከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድና መርሃ-ግብርን በተመለከተ የሁሉም ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ የሚመለከታቸው አካላት እያንደንዱን አስፈጻምና ፈጻሚ አካላትን ሃላፊነት በዝርዝርና በግልጽ በማስቀመጥ ረቂቅ እቅዱን በውይይትና በምክክር በማዳበር ስምምነት ላይ በማድረስ ማጽደቅና በሚያስፈልግበት ጊዜም እቅዱን መከለስ አለበት፡፡

129 ባለስልጣን መ/ቤቱ በሀገር ደረጃ የሚያዘጋጀው የከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ሁሉ በዳብደቤ በማድረስና በአፈጻጸሙ ላይ በተቀመጠው አመታዊ ፕሮግራም መሰረት መሆኑን አፈጻጸሙ ላይ ከእቅድ ጋር ንጽጽር በማድረግ ግምገማ በማድረግ በዩኒሞዳል ወደ ሀገር እየገቡ ያሉ ገቢ ዕቃዎች ላይ በአግበቡ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

130 ባለስልጣን መ/ቤቱ በጸደቀው አመታዊ እቅድና መርሃ-ግብር መሰረት ለሚያስገቡ አስመጪዎች፣የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎችን ለማበረታታት በየጊዜው ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና መስጠት አለበት ፡፡

131 በሀገር ደረጃ ከጸደቀ መርሃ-ግብር ውጪ የሚያስመጡና በተቀመጠላቸው ጊዜ ገዳብ ውስጥ ዕቃዎቻቸውን ከባህር ወደብ የማያነሱ አስመጪዎች ተለይተው ማስረጃው በመያዝ ሀገሪቱን ለማይገባ የውጭ ምንዛሪ እንዲትዳረግ ያደረጉ ድርጅቶችን ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ/ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማደረግ አለበት፡፡

132 በባለስልጣን መ/ቤቱ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች፣ዕቃ አስተላለፊዎችና የመርከብ ወክሎችን በተመለከተ መረጃዎቹ ተለይተው በየጊዜው በማሰበሰብና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላትም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ሪፖርት በማቅረብና አፈጻጸሙ ላይም ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

133 ባለስልጣን መ/ቤቱ ባህር ወደብ ላይ ከ8 ቀናት በላይ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ (የዕቃው ባለቤት፣የዕቃው

አይነት፤መጠን፤የቆይታ ጊዜና የቆዩበት ምክንያት) የሚያዝበት አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ለቆዩበት ምክንትና ለችግሮችን መፍተሄ መስጠት አለበት፡፡

134 በዩኒሞዳል ሥርዓት የሚገቡ ዕቃዎች በባህር ወደብ ላይ ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ በመቆየታቸው ሀገሪቷ በዲመሬጅ ምክንያት በየዓመቱ የሚታጣውን የውጭ ምንዛሪ ክፍያን በተመለከተ መረጃዎቹ ከሌሎችም የመንግሥት መ/ቤቶች ጋር ቅንጅት በመፍጠር እንድያዝ በማድረግ፤ በሀገር ደረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ ለመንግሥት አካል ጉዳዩ መፍተሄ እንዲያገኝ ማቅረብ አለበት፡፡

135 በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል ሀገራዊ የሆነ  የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለመደገፉና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊና ቀጠይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ በለመዘርጋቱ በየዕለቱ በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር መረጃ (የዕቃው ባለቤት፤ ዓይነት፤መጠን፤ የገባበትና የወጣበት ጊዜ እና በኦፐሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን) በመለየት ወቅታዊ የሆነ መረጃ መያዝ አለበት ፡፡

136 በዩኒሞዳል የገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ በባህር ወደብ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ እቃዎቻችውን የማያነሱ አስመጪዎች ከሚመለከታቸው አካላት መረጃውን በየወቅቱ በመሰበሰብና በማደረጅት አስመጪዎቹን በመለየትና ተገቢ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡


137 በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል በባህር ወደብ ላይ የተተዉ እቃዎችን ሁኔታ በቅድሚያ ተለይተው ዝርዝር መረጃዎችን በመሰበሰብና በመጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ተደረገው በወቅቱ ወደ ሀገር እንድገቡና እቃዎቹ ከብልሽትና ሀገሪቱን አግባብ ያልሆነ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ እንዳትደረግ ማደረግ አለበት፡፡

138 ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነቶችን በባህር ወደብ ከመድረሱ  አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪዎች  የዕቃ አስተላላፊ፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን፣  በአገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት በየጊዜው በማሰበሰብ አስመጪዎች ዕቃዎቻቸውን በወቅቱ እንድያነሱ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመርከብ መደራረብና የመኪና እጥረት ማስቀረት አለበት፡፡

139 ሀገሪቷ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ያጸደቀችሁን የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም ስምምነትን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከባለወደቡ ጋር ድርድር በለመደረግ ስምምነቱን ማሻሻል አለበት፤

**አባሪ-1**

## የማሪታይም ባለሥልጣን መዋቅራዊ አደረጃጀት



## አባሪ-2

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)**

**<u>የኦዲት አካባቢ</u>፡- "በአገሪቱ ገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ"**

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| I. የሀገሪቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን የትራንዚት አገልግሎት አሰጣጥ በቁጠባ፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡ | 1. ባለስልጣኑ የከፍተኛ መጠን ጭነትን (Bulk Shipments) በተመለከተ ከአስመጪዎች መረጃዎችን በማሰበሰብና በመተንተን በየበጀት ዓመቱ የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) አመጣጥ መረሃ- ግብር ረቂቅ ዕቅድ በመዘጋጀት ከአስመጪዎች ፣ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ሊያጸድቅ ይገባል፡ |
| | 2. ባለስልጣኑ የጸደቀውን የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድን (National Bulk Shipments plan) ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ሁሉ በወቅቱ በማሰወቅ በአፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ባለስልጣኑ የጸደቀውን የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና መረሃ-ግብር መሠረት ለሚያስገቡ አስመጪዎች፣የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 4. ባለስልጣኑ ከጸደቀው ዕቅድ እና መርሃ-ግብር ውጪ ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) ያስመጡ አስመጪዎች በመለያት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ለትራንስፖርት ሚኒስቴሩ አቅርቦ በማስወሰን በአፈጻጸሙ ላይ ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ባለስልጣኑ በየወሩ አስመጪዎች ዕቃዎቻቸውን እንዲያነሱ በተደረገው ጥረት ውስጥ ምን ያህል መጠን ዕቃ ከወደብ እንደተነሳ፣የተገኙ ውጤቶች እና ያጋጠሙ ችግሮችን በግልጽና በመለየት (የአፈጻጸም ሪፖርት) ለትራንስፖርት ሚኒስቴር እና |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 6. ባለስልጣኑ በባህር ወደብ ላይ በወቅቱ የማይነሱ የገቢና የወጪ ዕቃዎችን በተመለከተ ከችግሮቹ በመነሳት የፖሊስ ወይም የአሰራር ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮችን በጥናት በመለየት አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን በመስቀመጥ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር በማቅረብና በማስወሰን በአፈጻጸሙ ላይ ክትትል ሊያድረግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ባለስልጣኑ የዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎችን የአገልግሎት አሰጣጥን ስታንደርድን በመዘጋጀት የድርጅቶቹን አገልግሎት አሰጣጥ እና ታሪፍ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 8. ባለሥልጣኑ የገቢ ዕቃዎች በተመለከተ የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ስታንደርድና የትራንዚት ወጪ ስታንደርድ በመዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 9. ባለስልጣኑ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረገ አካልን በመከታተልና መረጃ በመሰበሰብ ተጠያቂ የሚሆኑበት የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ሊያቀረብ ይገባል፡፡ |
| | 10.ባለስልጣኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ መጠን ጭነትን (Bulk Shipments) ከግዥ ጀምሮ ያለውን የሎጅስቲክስ ሰንሰለት ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያድርግ ይገባል፡፡ |
| | 11.ባለሥልጣኑ በሀገር ውስጥ የጉምሩክ ማስተላለፊያ ቦታዎች የሚሰጡትን አገልግሎቶች በተቀላጠፈ መልኩ መከናወኑን ለመቆጣጠር የሚያስችል የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 12.ባለስልጣኑ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ ዕቃዎችን የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለይተው መፍትሄ ለማስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ |

| የኦዲት ጭብጥ Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria |
|---|---|
| | ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13.ባለስልጣኑ ጭነቶቹ ባህር ወደብ ከመድረሳቸው ከአንድ ሳምንት በፊት /Expected Arrival Time/ የባህር አጓጓዦችና መርከብ ወኪሎች ለአስመጪው እና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማሳወቃቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| II. ባስልጣኑ የሀገሪቱ ገቢና ወጪ ዕቃዎችን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና ተግባር ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡ | 14.ባለስልጣኑ አሰፈላጊ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ማዕከል (on line data base) ሊያደረጅ ይገባል፡፡ |
| | 15.ሀገሪቱ በየዓመቱ ወጪ የሚታደርገውን የዲመሬጅ ክፍያን በተመለከተ ባለስልጣኑ በዝርዝር መረጃዎችን በመከታተልና በማሰበሰብ በየዓመቱ ሊያደረጅ ይገባል፡፡ |
| | 16.ባለስልጣኑ ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር (ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች) በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን መጠን፣ ዓይነት፣የቆይታ ጊዜ እና በኦፐሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት መረጃዎቹን ሊያጠናቅር ይገባል፡፡ |
| | 17.ባለስልጣኑ የገቢ ዕቃዎች እና የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) የትራንዚት ትራንፖርትን በተመለከተ ባበህር ወደብ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር፣ ምክክር እና የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት በማደረግ ሊከታተልና ሊያሻሽል ይገባል፡፡ |
| | 18.ባለስልጣኑ በዕቃ አስተላላፊነት ውክልና በመርከብ ውክልና |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | አገልግሎት መስክ የተሰማሩና የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የተሰጣቸው ድርጅቶችን ወቅታዊ መረጃ በማደራጀት ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሊያሰረጭ ይገባል፡፡ |
| | 19.ባለስልጣኑ በተደጋጋሚ ድጋፍ ተደርጎላቸው በባህር ወደብ ላይ እቃዎችን በ30 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ በየወቅቱ በማጠናከር እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት በማድረግና በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 20.ባለስልጣኑ በባህር ወደብ ላይ ከ30 (ከሰላሳ) ቀናት በታች፤ከ30 (ከሰላሳ) ቀናት በላይ እና ከ6 (ከስድስት) ወራት በላይ ለቆዩ የገቢ ዕቃዎችን በመለየት በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በተቀመጠላቸው የትራንዚት ፕሮስጀር መሠረት ተግባራዊ እንድሆን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 21.ባለስልጣኑ የተተዉ እቃዎች በወቅቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማሰበሰብና በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት በጊዜው ማሰወቅ እና እቃዎቹ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 22.የከፍተኛ መጠን ጭነት የባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት አስመጪዎች የዕቃ አስተላላፊ፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን፣ በአገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዘን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት ለባለሥልጣኑና ለሚመለከታቸው አካላት ሊቀረብ ይገባል፡፡ |
| | 23.ባለሥልጣኑ አስመጪዎች ከዕቃ አስተላላፊ እና ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያ አጓጓዡን ጋር የገቡትን የውል ስምምነትና በተቀመጠላቸው መረሃ-ግብር መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 24.ባለስልጣኑ የወደብ ፕሮግራምና ተዛማች መረጃዎችን (ወደብ ዝግጁ መሆኑን፤ተለዋጭ ጊዜ መኖሩን፤አማራጭ የትራንዚት ኮሪደርና ሌሎች የሎጅስቲክስ አቅርቦቶች ) ለአስመጪዎች በወቅቱ ሊያቀረብ ይገባል፡፡ |
| | 25.ማናቸውም በየብስ ወይም በባህር ተጓጉዞ ወደ ሀገር የገባ ዕቃ ወደ ጉምሩክ መጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈፅሞበት ከጉምሩክ መጋዘን መውጣቱን ባለስልጣኑ ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 26.ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ከተፈፀመበት በኃላ በ7 ቀን ውስጥ ካልወጣ ወደ ባለስልጣኑ የተተዉ ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን እንዲዛወር ተደርጎ ወዲያውኑ እየተወገደ መሆኑን ባለስልጣኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 27.ባለስልጣኑ በየወቅቱ የገቢ ከፍተኛ ጭነት አፈጻጸም ግምገማን በተመለከተ ከአስመጪዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |

## አባሪ-3

**የሥራ ሂደት መግለጫ/ Process Description**

ከሁሉም አስመጪዎችና ከሚመለከታችው አካላት ለግብዓት የሚሆን ህጋዊ የእቅድ ማስረጃዎችን ማሰበሰብ

↓

ሀገራዊ የከፍተኛ መጠን ጭነትን አመታዊ ዕቅድ እና መርሃ-ግብር መዘጋጀት

↓

ዕቅድን ከባለድርሻ አካላት ጋር ስምምነት ላይ በማድረስ መጽደቅና ለሚመለከታቸው አካላት ሕጋዊ በሆነ መልኩ መድረስ

↓

ከግዥ ጀምሮ በዩኒሞዳል የሚገቡ ገቢ ዕቃዎችን መረጃ መሰብሰብና መደረጃት

↓

ባህር ወደብን በአግባቡ ለመጠቀምና የመርከብ መደራረብ ለመስወገድ የወደብ አጠቃቀም ፕሮግራም መውጣትና ተግባራዊ መድረግ

↓

የጫኑ መርከቦችና በባህር ወደብ የተከመቹ ገቢ ዕቃዎች ከተወሳነላችው ጊዜ በላይ እንደይቆዩ ክትትልና ቁጥጥር በመድረግ ድጋፍ መስጠት

↓

በአፈጻጸሙ ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋር ተገቢ የሆነ ግምገማ በመድረግ በጽሁፍ ለሚመለከታችው ግብረ-መልስ መስጠት

↓

ከዕቅድ ውጪ ያስገቡትን አስመጪዎች ተገቢውን እርምት እርምጃ እንዲወሰድ መድረግና የላቀ ሥራ ለሚሳዩ ዕውቅና

↓

የከፍተኛ መጠን ጭነቶች በታሰበው ጊዜ ለታሰበው ዓላማና አገልግሎት እንዲደርስ ማድረግ ትራንዚት ጊዜና ትራንዚት ወጪ መቀነስ

አባሪ- 4

## በተመረጡ እቃዎች ላይ እ.ኤ.አ ከጥር 2012 እስከ ሰኔ 2013 የስቶሬጅና ተዛማጅ የወደብ ክፍያዎች

| No | Type of Cargo | Port Due (USD) | Storage Charges (USD) | Other Costs (USD) | Total Payment (USD) | Owner of the Cargo |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Steam Coal | 582,292.8 | 268,598.8 | 759,179.3 | 1,610,070.81 | Ethiopian petroleum Supply Enterprise |
| 2. | Sugar | 753,546.8 | 559,897 | 3,214,126.6 | 4,527,570.4 | Sugar Corporation |
| 3. | Wheat | 781,616.9 | 41,628.1 | 5,750,104.8 | 6,573,349.8 | Ethiopian Grain Trade Enterprise |
| 4. | Fertilizer | 1,383,319 | 117,988.1 | 2,352,912.2 | 3,854,219.8 | Agricultural Input Supply Enterprise |
| 5. | Steel | 535,182.5 | 577,072.8 | 1,869,419.4 | 2,981,674.7 | A.A. Housing Development Project |
| 6. | Edible Oil | 894,699.3 | 7,360,016.3 | 10,720,997 | 18,975,712.6 | Merchandise & Wholesale Import Trade Enterprise |
| 7. | **Sub Total** | **4,930,657.30** | **8,925,201.10** | **24,666,739.30** | **38,522,598.11** | |
| **Project Cargo** | | | | | | |
| 8. | Fincha | 84.2 | 18,204.8 | 24,887.1 | 43,176.1 | Sugar Corporation |
| 9. | Methara | 6,234.5 | 54,363 | 76,349.8 | 136,947.3 | Sugar Corporation |
| 10. | Tendaho | 1,371 | 11,138.7 | 24,007.6 | 36,517.3 | Sugar Corporation |
| 11. | METEC | 214,035.1 | 1,591,809 | 2,097,760.6 | 3,903,605.4 | METEC |
| 12. | **Sub Total** | **221,724.8** | **1,675,515.50** | **2,223,005.10** | **4,120,246.10** | |
| | **Grand Total** | **5,152,382.10** | **10,600,716.60** | **26,889,744.40** | **42,642,844.21** | |